# አብርሃም

## ፈር ቀዳጁ

የኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 12 - 20 ታሪክ


በኪቲ እና ግሪፊትስ

ሥዕል በ«ዊሊ»

ትርጉም:- በኃይሉ ልመንህ

እርማት:- ዮዲት ኃይሉ እና ተመስገን ሁሴን

ዋና አርታኢ:- ዘነበ ገብረሐና



BIBLE BASED BOOKS

SIM PUBLISHING

የአሳታሚው መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

Copyright

© 2006 by SIM, Addis Ababa.

Originally published in English under the title of

**ABRAHAM, the Pioneer.**

Copyright © Kitty Anna Griffiths, 1977

Bible Stories Alive. A division of A visit with Mrs. G. Ministries Inc. 2851 St. Clair Avenue East, Toronto, Ontario, Canada M4B 1N4

**1ኛ እትም፣ 1999 ዓ.ም (2007)**

**አሳታሚ:- የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ**

**የፖ.ሣ.ቁጥር 127**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

**ስልክ 011 - 349 - 3252፣ 011-653 -3084፣**

**011-551-2973**

E-mail:SIMmedia@ ethionet.et

**የኮምፒውተር ጽሑፍ:- ጥሩ ወርቅ በቀለ**

**ሌይ አውት:- ዓለምፀሐይ እውነቱ**


BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING



# ታሪኮች

1. የአብርሃም ቤተ ሰቦች ....................5
2. የእስማኤል ታላላቅ ተስፋዎች ....................20
3. አብርሃም፣ የእግዚአብሔር ፈር- ቀዳጅ ....................34
4. የልዕልት ሦራ ስሕተት ....................47
5. የሎጥ ምርጫ ....................59
6. የአብርሃም እንግዶች ....................73
7. የሁለቱ ከተሞች አስፈሪ ወግ ....................89
8. አብርሃም ሰፈሩን ነቅሎ ተጓዘ ....................106

ታስታውሳላችሁ. . . ?....................120






# 1

# የአብርሃም ቤተ ሰቦች

ታላቁ አባት አብርሃም ይኖርበት በነበረ በኬብሮን አጠገብ በሚገኘው መምሬ ወደ ተባለው ስፍራ ደረስሁ:: ምንም እንኳን አብርሃምን በጨረፍታ እንኳ ማየት መልካም ቢሆንም፣ በዚህ ጊዜ ግን ላየው አልፈለግሁም ነበር:: እኔ ላያትና ላናግራት የፈለግሁት ሚስቱን ልዕልት ሦራን ነበር::


በዚያ ስፍራ የሥነ ምግባር መጽሐፌን በቦርሳዬ ውስጥ ይገኝ ነበር:: ታዲያ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለብኝ፣ ከዚህ መጽሐፍ የተገነዘብኩት የጨዋ ተግባር፣ አንድ ሰው እስከሚያየኝ ድረስ፣ በልዕልት ሦራ ድንኳን አቅራቢያ ከታላላቆቹ ዛፎች መካከል በአንዱ ሥር መቀመጥ ነበር:: (ቢያንስ ወንድ እንግዶች ሁልጊዜ የሚያደርጉት ይህንኑ ነበር::)

ሴት በመሆኔ በዚህ ስፍራ ተቀምጬ ሲያዩኝ ሥራ የምፈልግ ሊመስላቸውና እንድሠራ ወደ ቤተሰባቸው ሊወስዱኝ ያስቡ ይሆናል:: በዚህ ሰዓትና በዚህ ስፍራ፣ አንዲት ሴት በቤተሰብ ውስጥ ካልሆነች በስተቀር ችግር

ያጋጥማታል። ነገር ግን፣ ይህንን ወዲያውኑ አስረዳቸዋለሁ።

ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ካዩኝ ነው!

የሦራ ድንኳን ልክ እንደ አሁን ዘመን የቤድዊን ዘላን አረቦች ድንኳን፣ ከጥቁር የፍየል ጠጉር ተፈትሎ የተሠራና በውስጡ ልዩ ልዩ ክፍሎች ያሉት ነበር። በአቅራቢያው፣ በመቶ የሚቆጠሩ ሌሎች ብዙ ድንኳኖች ነበሩ። የልዕልት ሦራ መሆኑን በማውቀው በዋናው ድንኳን ፊት ለፊት ካለው ዛፍ ሥር ቁጭ አልኩ።



የሰዎች ፊት በድንኳኑ በር ላይ ብቅ ይልና ወዲያው ይጠፋል። የሰዎች ሣቅ ደግሞ ይሰማኛል። ታዲያ ይህ ሁሉ ተስፋ አላስቆረጠኝም። ወደ ድንኳኑ ውስጥ ገብቼ ልዕልት ሦራን ለማነጋገር ወስኜ ነበር። ይህ ካልሆነ ደግሞ፣ እርሷ እንድታናግረኝ ፈልጌ ነበር።



ቆይ ቆይ እስቲ፣ አንድ ሰው ወደዚህ እየመጣ ነው፦ ቆንጆ ወጣት ናት፣ ግብፃዊትም ትመስላለች።

«እመቤቴ በቂ አገልጋዮች አሉን ትላለች፤ ሆኖም የምትጠጪው ውኃና የምትቀምሺው ምግብ ላመጣልሽ እችላለሁ። በዚህ ስፍራ ብቻሽን መቆየት የለብሽም። ስለዚህ ወደ መጣሽበት ስፍራ በደህና እንደምትመለሺ ተስፋ አለኝ» አለችኝ።

«ይህንኑ ያህል እኔም አስቤ ነበር፣» አልኩኝ ለራሴ መልሼ። ከዚያም ድምፄን ከፍ አድርጌ፣ «ለልዕልቲቱ እኔ ሴት መሆኔን ንገሪያት፤ ነገር ግን እንደ ገረድ ሳትቆጥረኝ ለደቂቃ ያህል ወዳለችበት ገብቼ እንዳነጋግራት ትፈቅድልኝ እንደ ሆነ ጠይቂልኝ» አልኳት።

«አንቺ ማን ነሽ? ከየት ነው የመጣሽው?» ብላ ግብፃዊትዋ ሠራተኛ ጠየቀችኝ።

«እኔ ወይዘሮ ጂ. እባላለሁ፤ የመጣሁትም፦ ከክርስቲያን ዘመን ሁለት- ዜሮ- ዜሮ- ዜሮ (2000) ነው» አልኳት። «ሆኖም ይህንን ለማስታወስ ያስቸግርሻል፤ ብቻ አንድ ሰው ሊያነጋግራት እንደሚፈልግ ለልዕልቲቱ ንገሪያት። ስለምጠጣውና ስለምበላው ምግብ አትጨነቂ። ያ ወደ ውስጥ በምገባበት ጊዜ ይደርሳል» አልኳት።

ከዚያም ወጣትዋ
ግብፃዊት ተመልሳ ወደ
ድንኳኑ ገባች::



ወዲያውኑ እንደገና
ወጣችና፣ «ተከተዪኝ»
አለችኝ:: እናም እየተመራሁ
በግቢው ውስጥ ወዳለው
ትልቅ ድንኳን ተወሰድኩ::

እዚያም አንዲት
ሰማያዊ ልብስ የለበሰች
ቆንጆ አዛውንት ሴት ቁጭ
ብላ ቀይ ያንገት ልብስ ትጠልፋለች:: የሸመና ዕቃዋም
አጠገብዋ ነበር:: እንዳየችኝ በጥሩ ሁኔታ ሰላም አለችኝ::

«በወጣትነት ዕድሜዋ እጅግ ውብ እንደ ነበረች
የአሁኑ ገጽታዋ ይመሰክራል» አልኩ ለራሴ:: ቀደም
ብሎም ስለ ውበትዋ ብዙ ጊዜ የሰማሁት ሐሰት
አልነበረም:: ዛሬ ግን ፊቷ መሥመሮችን አውጥቷል::
በተለይም በአፍዋ አካባቢ የሚታዩት መሥመሮች
ጥቂት አስተከዙኝ::

«የምትጠጪው ወተት ላምጣልሽ፣ ጥቂት
አቾሎኒና ፍራፍሬዎችንስ አትበዪም?» አለችኝ::

ከዚያም ወለሉ ላይ ቁጭ ብዬ የፍየል ወተት እጠጣ
ጀመር:: ጣፈጠኝ:: ከቀረበልኝ አቾሎኒና ተምርም
በላሁ::



ከዚህ በኋላ ፍርሃት ለቀቀኝ:: እናም፣ «ልዕልት
ሣራ፣ ስለ ድፍረቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ይህንን
የማደርገው ግን ስለ ተገፋፋሁ ነው አልኳት::»

«አየሽ ልዕልት ሣራ፣ እኔ ባለሁበት ስፍራ ለሚገ
ኙ ብዙ ጓደኞቼ ታሪኮችን እተርክላቸዋለሁ:: ስለዚህ
የታዋቂውን የባልሽን የአብርሃምን ታሪክ መተረክ
አለብኝ:: ነገር ግን፣ ለመተረክ ታሪኩን ከባለ ታሪኮቹ
በቀጥታ መስማት ያስፈልገኛል::»


«እርሱ ታዋቂና አስደናቂ ሰው እንደ ሆነ
አውቃለሁ:: ብዙ ሰዎችም ስለ እርሱ ታሪክ ጽፈዋል::
ሆኖም፣ እኔ ያነበብኩዋቸው ሁሉ ፍሬ ነገሩን ያልያዙ
ናቸው::»

«አየሽ፣ ልዕልት እርሱ፣ በመጽሐፍ ቅዱሳችን
ውስጥ <የእግዚአብሔር ወዳጅ> ተብሎ ተጠርቷል::
ስለዚህ ሁሉም ሰው እጅግ አስደናቂ እድርጐ
ሊያቀርበው ይፈልጋል:: ሣራ፣ እርሱ አስደናቂ ሰው
አይደለም ማለቴ አይደለም፤ ችግሩ ሰዎች አብርሃምን
ከእግዚአብሔር ጋር ያምታቱታል:: ከዚህ የተነሣ
አንዳንድ ጊዜ ስለ እርሱ የሚባለው ነገር እውነት
የማይመስልና ሐሰትን የተላበሰ ነው::»

ልዕልት ሣራ፣ «እርሱ እጅግ የሚደነቅ ሰው ነው»
አለችና ግብፃዊቷን አገልጋይ «አጋር፣ እስቲ ወደ ውጪ
ሂጂና ከጉድጓዱ ውስጥ ውኃ ቀድተሽ ነይ:: እዚህ

ቆመሽ የምንነጋገረውን መስማት እኮ የለብሽም:: በይ አሁን በፍጥነት ሂጂ!» ብላ አዘዘቻት::

«እመቤቴ፣ አንቺ የምታደርጊውን አደረግሁ እንጂ ምን የተለየ አደረግሁ:: አንቺስ ብትሆኚ ስለምትጠራጠሪ ተደብቀሽ የምንነጋገረውን ታደምጪ የለ:: አንቺም እኮ እንደዚህ እንዳታደርጊ ሲነገርሽ ሰምቻለሁ» ካለች በኋላ ግብፃዊትዋ አጋር እየተቆናጠረች የውኃ መቅጃ እንስራ ይዛ ወጥታ ሄደች::




እኔም «መታገስ አለብሽ:: ይህ ላንቺ በጣም ከባድ ነገር ነው:: «እኔ ብሆን አባርራት ነበር» አልኳት::

«አዎ፣ በእርግጥ ልታገሰውም የሚገባ ነገር ነው» አለች::

ልዕልቲቱ እነዚህን ነገሮች ለአንድ አፍታ እንኳን በቁጥጥር ሥር አድርጋ ታውቅ ይሆን? ብዬ ተገረምኩ::

ከዚያም፣ «ይህቺ አጋር የማትረባ ልጅ ናት:: ወደዚህ ባልመጣች ይሻል ነበር:: አሁን ግን ላባርራት አልችልም» ብላ ሣራ ስትናገር በሣራ ጉንጮች ላይ



እንባ ወረደ::

ጥቂት ጊዜ ጸጥ ካለች በኋላ፣ «በነገራችን ላይ፣ ሣራ ብለሽ አትጥሪኝ:: ስሜ ሦራ ነው:: ስጠራ የቆየሁትም ሦራ በሚለው ስም እንጂ ሣራ ተብዬ አላውቅም:: ስሜ ሦራ ነው::» አለችኝ::

«እህ፣ ይቅርታ አድርጊልኝ፣ ልዕልት ሦራ፣» አልኳት::

«ወደዚህች የማትረባ ልጅ ነገር ብመለስ» (ይህን ስትል ልዕልትዋ ፊትዋ በቁጣ ተለውጦ ነበር)፣ «ከባለቤቴ ልጅ ስለ ወለደች፣ ላባርራት አልችልም::»

«በእርግጥ፣ የራሴ ስሕተት ነው:: አየሽ ወይዘሮ ጂ.፣ እኔ እግዚአብሔርን ለመከተል የሚጥርን ሰው የምከተል ሴት ነኝ:: ይህ ነገር ለእርሱ አዲስ ነው:: እግዚአብሔር ከብዙ ዓመታት በፊት አስደናቂ ተስፋዎችን ገብቶለታል:: ታዲያ፣ እነዚህ ተስፋዎች ሳይፈጸሙ ሲቆዩ ትዕግሥት አጣን:: ከዚያም አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ብዬ አሰብኩ፤ ያ ግን ትልቅ ጥፋት ነበር!


በዚህን ጊዜ ልዕልትዋ እየተቆጣች ሳይሆን እያለቀሰች ነበር::

«ይቅርታ አድርጊልኝ፣ እንደዚህ መሆን አልነበረብኝም፤ ታሪኩ ከየት እንዲጀመር ነበር የፈለግሽው?» ስትል ጠየቀችኝ::

«እህ፣ እባክሽን ከመጀመሪያው ጀምረሽ ንገሪኝ፣ ማለትም ትንሽ ልጅ ሆነሽ ካለው ታሪክ ጀምረሽ ተርኪልኝ» አልኳት::

ልዕልት ሦራ መልሳ፣ «እኔ እኮ ዛሬ ሰማንያ ዘጠኝ ዓመቴ ነው» አለች::

«ምን? እህ፣ ይቅርታ አድርጊልኝ! እኔ አላምንም:: ግን እኮ አሁንም በጣም ቆንጆ ነሽ:: የሰማንያ ዘጠኝ ዓመት ሴት አትመስይም» አልኳት::



«ውበቴማ ለረጅም ዓመታት ሲነገርለት የቆየ ነው፣» አለች ልዕልት ሦራ ያለ እንዳች መታበይ:: «ሆኖም፣ አስቸጋሪ ነበር::» (እኔም ብሆን በአእምሮዬ ውስጥ ሳላኖረው አልቀረሁም:: በእርግጥም እውነት ነበር!)

ወዲያውኑ፣ አንድ ዕድሜው አሥራ ሁለት ዓመት የሆነ ልጅ እየሮጠ መጥቶ ወደ ልዕልት ሦራ ድንኳን ውስጥ ገባ::

«እስማኤል፣ ወደዚህ



እንደርድሮ የሚያስገባ ምንም ሥራ የለህም!» አለችው ልዕልት::

«አንተም እንደ እናትህ ሥነ - ሥርዓት የለህም::»

ልጁም እኔን እንዳየ ደንግጦ ባለበት ቀጥ ብሎ ቆመ::

እኔም ፈገግ አልኩለት፤ የእርሱም ጥቁር ዓይኖች መልሰው በፈገግታ ወደ እኔ አበሩ:: ደፋርና ጠንካራ ልጅ ነው:: የለበሰው ብሩህ ቀለም ያለው ካናቴራ መሰል ነገር ብቻ ነበር::

«አሁን ምን ትፈልጋለህ?» አለችው::

«አባቴን እየረዳሁት ስለ ሆነ ለእርሱ የሚሆን የምፈልገው ነገር አለ» አለና እስማኤል የተጠቀለለ ገመድ ብድግ አድርጎ ልዕልትዋን በማሾፍ መልክ እያየ፣ ወጥቶ እንደገና ሄደ::

«አየሽው? ይህን ትንሽ ለማኝ! እኔ ምንም ላደርግ አልችልም:: አባቱ በጣም ይወደዋል:: በዚህ ምክንያት እርሱም፣ «አባቴ እንደዚህ፣ አባቴ እንደዚያ» ይላል:: ይህ እርጉም ልጅ አባቱን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎታል:: ጆሮዎቹን በጥፊ ባግለው ደስ ይለኛል::

«ቅድም ውኃ እንድታመጣ የላኳት ያቺ ባለጌ እናቱም ትዕቢተኛ ናት:: የእርሷ ነገር በጣም ያሳዝነኛል:: ግን ምን ላድርግ፣ ችዬው መኖር አለብኝ:: እኔው

በገዛ እጄ ያደረግሁት ነው፡፡ አድሮ የሚመጣውን ጣጣ ልብ አላልኩትም ነበር፡፡ እነርሱ ለባሌ አስፈላጊ ሰዎች ናቸው- በተለይ ልጁ፡፡ እናቱም ብትሆን ለባሌ አስፈላጊው ብትሆንም፣ እኔ ግን አስፈላጊ ናት ብዬ ማሰብ አልፈልግም፡፡»

«አክስቴ፣አጐቴ አብርሃም አለ እንዴ? አንቺን ስታወሪ ስለ ሰማሁ፣ መኖርሽን አውቄያለሁ» የሚል ዕድሜው ወደ ሃምሣው የሆነ ሰው አንገቱን ወደ ድንኳኑ ውስጥ ገባ አድርጐ ታየ፡፡

«ኦ፣ ሎጥ!» ብላ ልዕልትዋ ከመቀመጫዋ ብድግ አለችና፣ «እንኳን ደህና መጣህ፣ ልጄ» አለችው፡፡



«አክስቴ፣ እኔ እኮ ልጅ አይደለሁም» እያለ ልዕልቷን ሳማት፡፡

«አንተ ለእኔ ሁልጊዜ ልጅ ነህ፡፡ ጐረምሳው ልጄ» አለችው፡፡

«አባትህ ከሞተ በኋላ ያሳደግንህ አጐትህ አብርሃምና እኔ ነበርን፡፡ አይ! አባትህ የሞተው ያለ ዕድሜው ነበር፡፡ የሞተው እኮ ገና ከዑር



ከመምጣታችን በፊት ነበር፡፡ ወይኔ፣ ጊዜው እንዴት ይበራል! ለመሆኑ ዛሬ ምን እግር ጣለህ?»

«አንዳንድ ጊዜ አንቺን የምወድሽን አክስቴን መጠየቅ አለብኝ፡፡ አንድ በኬብሮን የምሠራው ሥራ ነበር፡፡ እንዲሁም ከአጐቴ አብርሃም ጋርም የምንመካከርባቸው አንድ ሁለት ጉዳዮች አሉኝ» አላት፡፡

«አጐትህ ሲያይህ ደስ ይለዋል፤ ሎጥ፣ ቤተሰብ እንዴት ነው?»

«ሁሉም ደህና ነው፡፡ ነገ ማታ በሰዶምና በጐሞራ ያሉትን ሰዎችን ሁሉ እንጋብዛለን፡፡ ሁሉም ሰው ታድሟል፡፡ ሚስቴም አምራና ደምቃ ትገኛለች፡፡

«በነገራችን ላይ በቤታችን ጐን አዲስ ክፍል ሠርተናል፡፡ አክስቴ አሁን ቤታችን በዑር የነበራችሁን ትልቁን ቤት ይመስላል፡፡»

«መቼም ሎጥ፣ ከዑር ምድር እንድንወጣ የጠራንን ያሕዌን እንደማትረሳ ተስፋ አለኝ፡፡»

«አየሽ አክስቴ፣ ስለ እኔ በመጨነቅ ጊዜሽን አታጥፊ፡፡ ይልቅስ ስለ ራስሽ አስቢ፡፡ በይ እንግዲህ መፍጠን አለብኝ፡፡ አጐቴ አብርሃም የት ነው የሚገኘው ነው ያልሽኝ?» አለና ሎጥ እየተጣደፈ ወጥቶ ሄደ፡፡

«ስለ ወንድማችን ልጅ ስለ ሎጥ መጨነቄን ማቆም አልችልም» አለችና ልዕልት ሦራ ተነፈሰች፡፡

ከዚያም አንድ ሠራተኛ የተጻፉ ዝርዝር ነገሮችን ይዞ ወደ ውስጥ ገባ፣ «እመቤቴ አስቤዛችንን እየተመለከትኩ ነው:: ነገ ኬብሮን ወዳለው ገበያ እሄዳለሁ:: ስለዚህ የሚያስፈልግሽን ነገር ትነግሪኛለሽ?» አላት::



እርሷም፣ «ጨውና ቅመማ ቅመም ያስፈልገኛል ኤሊዔዘር:: ደግሞም ለወተት መናጫ የሚሆን አዲስ ቆዳ እፈልጋለሁ:: ለዳቦ መሥሪያ የሚሆን የስንዴ ዱቄት፤ እንዲሁም የደረቀ ፍራ ፍሬ ያስፈልገኛል:: አህ፣ አጋር የውኃ እንስራዋን ሰብራለች:: ስለዚህ ሁለት እንስራዎችን ትገዛልኛለህ ኤሊዔዘር:: እንግዲህ፣ የቀረውን ነገር ላንተ እተወዋለሁ:: ምን እንደሚገዛ አንተ ታውቃለህ» አለችው::

ከዚያም ኤሊዔዘር ወጥቶ ሄደ::

«ኤሊዔዘር ባይኖር ኖሮ ምን እንደምናደርግ አላውቅም» አለች ልዕልቲቱ:: «ሕይወቱን በሙሉ ከእኛ ጋር ነው የኖረው:: ለኤሊዔዘር ሕይወትሽን



እንኳን አምነሽ ልትሰጪው ትችያለሽ:: እኛ አምነን ሰጥተነዋል! በመቶዎች የሚቆጠሩ አገልጋዮች አሉን. . .»

እኔም ቀበል አድርጌ፣ «በመቶዎች የሚቆጠሩ?» ስል በመገረም ጠየቅኋት::

«አዎ፣ ታሪኬን ስትሰሚ (ደግሞም ልተርክልሽ ተዘጋጅቻለሁ) ይህ ሁሉ እውነት መሆኑ ይገባሻል:: ቀድሞ እንደ ነገርኩሽ፣ እግዚአብሔርን ለመከተል እየሞከረ ያለን ሰው እየተከተልኩ ነው:: ውጣ ውረዶች አጋጥመውናል:: አብርሃም ባሌ ቢሆንም እንኳ፣ በአንድ በኩል ደግሞ ወንድሜ ነው::»

«ወንድምሽም፣ ባለቤትሽም ነው?»

ምንም ነገር አያስደነግጠኝም ብዬ የምኮራው እኔ፣ ግን በተናገረችው ነገር ደነገጥኩ::

«አዎ፣ አዎ፣ ወይዘሮ ጂ:: ባሕላችን እንዳልገባሽ አውቀአለሁ:: ታሪኩን ስቀጥል አስረዳሽና ይገባሻል::»

«አመሰግናለሁ ልዕልት ሦራ፣ አዎ ያኔ ይገባኛል» አልኩኝ ::

«እንዲህ ነው፣» አለች ልዕልት ሦራ፣ «እኔ ያደግሁት ሁለመናው ዘመናዊ በሆነው ዘመናዊ የዑር ከተማ ነው:: አባቴ ታራ ሀብታም ነበር:: እናቴን ከማግባቱ በፊት ሌላ ሚስት አግብቶ ነበር::

የመጀመሪያው ሚስቱ የአብርሃም እናት ነበረች፡፡ እርሷ ከሞተች በኋላ፣ የእኔን እናት አገባ፣ ከዚያም እኔ ተወለድኩ፡፡ ታራም የጨረቃ አምላክ የነበረውን ናናርን ያመልክ ነበር፡፡»

«እኔና አብርሃም እግዚአብሔር ለአብርሃም እስከ ተናገረው ጊዜ ድረስ ያደግነው ናናርን እያመለክን ነበር፡፡ በእውነትም እውነተኛው አምላክ አናገረው፡፡ ይህ ሁሉን ነገር ለወጠው፡፡ ሕይወታችን ውጣ ውረድ እና ተስፋዎች የሞላበት ነው፡፡»

ከዚያም ልዕልትዋ አፍዋን በእጅዋ ከልላ፣ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ፣ ከተስፋዎቹ አንዱ እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጠኝ ነበር፡፡ ግን አልሆነም፤ ስለዚህ. . . ስለዚህ. . . »


ይህኔ ልዕልትዋ በኀዘን በጣም ዛለች፡፡ እኔም እጅዋን ያዝ አድርጌ ጨመቅ ሳደርጋት፣ «እባክሽን ይቅርታ አድርጊልኝ» አለችኝ፡፡ ያኔ ምን እንደምመልስላት ግራ ገባኝ፡፡

ከዚያም «እባክሽን ሌላ ጊዜ ተመልሰሽ ነይ፡፡ ሌላም የማጫወትሽ ነገር አለኝ» አለች፡፡

«አዎ፣ እኔም እንደገና ብመጣ ደስ ይለኛል፡፡ ደህና ሁኚ፡፡ ልዕልት» አልኳትና መንገዴን ቀጠልኩ፡፡

ወደ ውጪ ስወጣም ግብፃዊትዋን የልዕልት ሠራን አገልጋይ አጋርን አገኘኋት፡፡ እኔን እየጠበቀችኝ ነበር፡፡





«እዚያ ያለውን ሰው ትመለከቺዋለሽ? እርሱ አብርሃም ነው፡፡ እርሱ የልጄ አባት ነው፡፡ ልጄም የእርሱ ወራሽ ነው፡፡ አየሽው?» አለችኝ፡፡

አጋር ቀጥ ያለ አቋም ያለውና እስማኤልን ጉት አድርጎ በሩቁ ይሄድ ወደ ነበረው ሰው በልዩ ደስታ ስሜት አመለከተችኝ፡፡

ሆኖም፣ በዚህን ጊዜ ከእርሷ ጋር ቆይቼ ልዕልትዋን ማማት አልፈለግሁም፡፡ ስለዚህ ልቆይ አልችልም አልኳትና በጥድፊያ ተለይቼአት ሄድኩ፡፡

«ይህ አስገራሚ ነው» አልኩ ለራሴ፡፡ «ይህ ጥሩ ታሪክ ሊወጣው ይችላል፡፡ ሳልሰነብት መመለስ አለብኝ» ባዬ አሰብኩ፡፡



# 2

# የእስማኤል ታላላቅ ተስፋዎች

እንደገና ወደ መምሬ ተመለሼ በመሄድ ላይ ሳለሁ አንድ የሚያፏጭ ነገር በቀኝ ጆሮዬ አጠገብ አለፈ:: ኘ ስስስስስት! ሌላውም እያፏጨ በግራ ጆሮዬ በኩል አለፈ:: ኘስስስስስት! ሁለቱም ነገሮች ከእኔ ጥቂት ሜትሮች ርቀው በመሬት ውስጥ ተቀረቀሩ::

የቀስት ፍላጻዎች ነበሩ!

እኔም፣ «ተው እንጂ እስማኤል፣ ምን ሆነሃል» ስል ጮኽኩ:: «አንተ ተንኮለኛ፣ መጥፎ ልጅ፣ ናና በትሕትና አነጋግረኝ:: ወይዘሮ ጂ.ን በፍላጻ ልተመታት እየሞከርክ ነው?»

እስማኤልም ከተደበቀበት ቁጥቋጦ ውስጥ እየሮጠ ወጣ:: ቀይና ብርቱካንማ ልብሱን ለብሶ ነበር::

«በእውነት አይደለም:: ወይዘሮ ጂ. ልመታዎት አልነበረም::» «በቀስትና በፍላጻ ውርወራ በጣም ጉበዝ ነኝ:: እኔ የፈለግሁት ፍላጻዬ እያፏጨ በጆሮዎት በኩል እንዲያልፍ ብቻ ነበር::»



«ራሴን አነቃንቄ ቢሆን ኖሮስ?» አልኩት::

«ጥሩ አይሆንም ነበር፣» አለኝ ለመሳቅ እየሞከረ:: «ዛሬ በፍላጻዬ የመታኋትን ተመልከቱ» አለኝ::

ከዚያም ክንፎችዋን የምታርገበግብ ዳክዬ አንጠልጥሎ እያሳየኝ፣ ሰብስቦ የያዛቸውን ትንንሽ ወፎችም አሳየኝ:: የቀስት ደጋኑን ትከሻው ላይ አንጠልጥሎ ነበር:: ፍላጻዎቹን ደግሞ በማኅደር አድርጎ በወገቡ አስሮአቸዋል::

«ይህች ዳክዬ አልሞተችም፣ እስማኤል ግደላት እንጂ!»



«ክንፎችዋን ስታርገበግብና ስትጮህ ደስ ይለኛል:: እንዲህ ስትሆን የሞተችውን ከጫካ ይዤ እንዳልመጣሁና በፍላጻ እንደ መታኋት ያሳያል» አለ::

«ይህን የምታሳየው ለማን ነው?»


«ለልጆቼ ነዋ::»

እኔም፣ «እስማኤል፣ ምስኪን ፍጥረትን እንደዚህ

ማሠቃየት ጭካኔ ነው፡፡ አንገትዋን ጠምዝዛት፣ ያለበለዚያ ግን እኔ እጠመዝዛታለሁ፡፡ ዳክዬዋን የምትገድላት ከሆነ በፍላጻ መምታትህ ምንም አይደለም፤ እንድትሠቃይ ግን አታድርጋት፡፡»

«አይ፣ አሁን ልገድላት አልፈልግሁም፡፡ በራስዋ ጊዜ ትሙት፡፡ ይልቅስ ወይዘሮ ጂ. ከፈለጉ ኑና እንስሳቶቼን ላሳይዎት፡፡ ራሴ የያዝኳቸው ብዙ የዱር እንስሳት አሉኝ፡፡»

«እስማኤል፣ የዳክዬዋን አንገት የምትጠመዝዝ ከሆንክ እመጣለሁ፡፡»



«እሺ፣ እጠመዝዛታለሁ፣» አለና ጠመዘዛት፡፡

ከዚያም አብሬው ሄጄ እንስሳቱን ላይለት ወሰንኩ፡፡

ቆይቶም፣ «ወይዘሮ ጂ. ዛሬ ወደ አሮጊቷ ሦራ ድንኳን አይሂዱ፡፡ እኔ ወደ አደን በሄድኩ ጊዜ እናቴና ሦራ በድንኳኑ ውስጥ ሆነው በኃይል ይጨቃጨቁ ነበር፡፡ በዚህ



ሁኔታ በጠዋት ጭቅጭቅ በሚጀምሩበት ጊዜ ሙሉ ቀን ይጨቃጨቃሉ፡፡ አንዳንድ ቀኖች ጥሩ አይደሉም- ብቻ እንደ ሁኔታው ነው፡፡

«አሮጊቷ ሦራ፣ እናቴን ታበሳጫታለች፡፡ ሆኖም፣ እናቴም የዋዛ ባለመሆንዋ ዋጋዋን ትሰጣታለች፡፡ አባቴም ሊያስቆማቸው አይችልም፡፡ አንዳንድ ጊዜ መጨቃጨቅ ሲጀምሩ በጣም ይጨንቀዋል፡፡ እኔ ግን፣ አባቴ ሲጨነቅ ማየት አልፈልግም፡፡

«ይህ ሁሉ ቢሆንም ግን፣ እኔና አባቴ ጥሩ ጊዜ አብረን እናሳልፋለን፡፡ አባቴን እወደዋለሁ፡፡ አባቴም ይወደኛል፡፡ እኔ የእርሱ ወራሽ ነኝ፡፡ ማለቴ፣ የእርሱ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው፡፡ አንድ ቀን የእኔ ይሆናል፡፡

«አሁን ግን ስለ እነዚህ ተጨቃጫቂ ሴቶች ማውራቱን እንተወውና፣ ወደዚያች አሮጊት ወደ ሦራ ድንኳን በመሄድ ፈንታ፣ አካባቢውን ላሳይዎት፡፡ ዛሬ ቀኑ የጭቅጭቅ ስለ ሆነ ወደዚያ አይሂዱ!»

«ያውቃሉ፣ ይህ ሁሉ የእናቴ ስሕተት አይደለም፡፡ እናቴ ከኑሮ ብዙም የምትጠብቀው ነገር አልነበራትም፡፡ በግብፅ አገር ወደዚህ ትልቅ ቤተሰብ ስትቀላቀል፣ እንዲት ተራ አገልጋይ ልጃገረድ ነበረች፡፡ በወቅቱ ረሃብ ስለ ነበር፣ አባቴ ለተወሰነ ጊዜ በግብፅ ቆይቶ ነበር፡፡ እናቴም ከአንድ ቦታ ወጥታ የአሮጊቷ የሦራ አገልጋይ ሆነች፡፡ ኋላ ግን እንደ ሚስት አድርጉ አባቴ አገባት፡፡

አሁን ታዲያ እኔን በመውለድዋ ሁኔታዋ ተሻሽሏል። እኔም የአባቴ ወራሽ ነኝ። ወራሽ ምን እንደ ሆነ ያውቃሉ?»

«አዎ፣ አውቃለሁ፣» አልኩት። «አባትህ በሚሞትበት ጊዜ ያለውን ሀብትና ንብረት ትወርሳለህ ማለት ነው። ሁሉም ነገር የአንተ ይሆናል።»

«ትክክል! እስክወለድ ድረስ፣ ኤሊዔዘር የአባቴ ወራሽ ነበር። እርሱ የአባቴ ንብረት አስተዳዳሪም ነው። ኤሊዔዘር ብልህ ሰው ነው። ይህን ሁሉ ሀብት ለመውረስ ይጠባበቅ ነበር። ሆኖም፣ ንብረቱንም የሚጠብቀው በመልካም ሁኔታ ነው። መጥፎ ነገር አይናገረኝም። ሆኖም ታዲያ እኔ የዚህ ሁሉ ሀብት ያለው ወራሽ ስለሆንኩ፣ የእርሱ ሊሆን አይችልም። የተረጋጋ፣ ጥሩ ሰው ነው። እኔ ግን እንደ ኤሊዔዘር ባለኝ ረክቼ ስለሌላው ግድየለሽ መሆን የምችል አይመስለኝም።»

«ኤሊዔዘር ከአባትህ ጋር ያለው ዝምድና ምንድን ነው?»

«ኧረ፣ ምንም ዓይነት ዝምድና የለውም፣» አለ እስማኤል። «አባቴ ልጅ ስላልነበረው ብቻ ኤሊዔዘርን ወራሹ እንዲሆን መረጠው። አሁን ግን አባቴ እኔን ወልዷል፣ ስለዚህም ወራሹ እኔ ነኝ።»

«አሀ፣ ገባኝ።»



«በሉ ኑ፣ ወደ እኔ ቦታ ደርሰናል። አባቴ ይህን ኩርማን መሬት እንደ ፈለግሁ እንዳደርገው ፈቅዶልኛል። ስለዚህ እኔም ለእንስሳት መኖሪያ ግቢ አደረግሁት።»

ከእንስሳቱም መካከል፣ በጋጣ ውስጥ ቀበሮዎች፣ ጥንቸሎች፣ ጃርት፣ ሁለት እባቦች፣ ልዩ ልዩ እንሽላሊቶች፣ ብዙ ወፎች ነበሩ። እንዲሁም እስማኤል የራሱ የሆኑ በረት ሙሉ በጐችና ፍየሎችም ነበሩት።



አሁን ያለነው ከድንኳኖች ውጪ በታላላቅ የዝግባ ዛፎች መካከል ነው።

«እስማኤል በዚህ ዕድሜህ ስለ ውርስ ብዙ የምታስብ ትመስላለህ፣» አልኩት። «ይህ በምን ምክንያት እንደ ሆነ ልትነግረኝ ትችላለህ?»

«ምናልባት ስለዚህ ብዙም ላላስብ እችል ነበር:: ስለዚህ አዘወትራ የምትነግረኝ እናቴ ናት:: ለነገሩማ ስለ ሌላ ስለ ምን ልታስብ ትችላለች? አገልጋይ ባሪያ ነበረች:: ዘመዶቿ በቅርብ የሉም:: ግብፃውያን ናቸው:: እኔን ከወለደች ጀምሮ ለአሥራ ሦስት ዓመታት ያህል ይህቺ አሮጊቷ ሦራ ልጅ ትወልድ ይሆናል ብላ ትሠጋለች:: ሦራ ልጅ ከወለደች ደግሞ ልጅዋ ዋነኛ ልጅ ይሆናል::

«ከአሁን ወዲያ ግን ስለዚህ ጉዳይ መጨነቅ አያስፈልግም:: እናቴ አትጨነቅም:: ስለ አሮጊቷ ሦራ መጨነቅ ትታለች:: ሦራ አርጅታለች:: ሦራ ልጅ ለመውለድ ከአሁን በኋላ አትችልም::»

«ለልዕልት ሦራ አዝናለሁ፣» አልኩ::

«እዚህ የሚኖሩ ቢሆን ኖሮ አያዝኑላትም ነበር:: ነዝናዛ አሮጊት ናት:: አባቴን ስትጨቀጭቀውና እናቴንም እንዴት እንደምታደርጋት ያዩና ይሰሙ ነበር:: አባቴም እናቴን መነዝነዟን እንድታቆም ማድረግ አለበት::



«እኔ ከመወለዴ በፊት፣ አሮጊቷ ሦራ ልጅ መውለድ ስለማትችል፣ እናቴ እኔን




ወልዳ እንድሰጣት ትፈልግ እንደ ነበር ያውቃሉ? (ስለዚህ ሁሉ እናቴ ነግራኛለች):: ከመወለዴ በፊት እናቴ እኔን ልትወልድ ስለ ነበረ በደስታ ትዘል ነበር:: አሮጊቷ ሦራ በዚህ በጣም ስለ ቀናችና ጨካኝ ስለሆነችባት፣ እናቴ ከእርሷ ሸሽታ በአንድ የውኃ ጉድጓድ አጠገብ አዝና ተቀመጠች::

«በዚያ ወቅት በውኃ ጉድጓድ አጠገብ አርፋ ወደ አገርዋ ወደ ግብፅ ተመልሳ ለመሄድ ያሰበች ይመስለኛል:: ነገር ግን ምን እንደ ሆነ ያውቃሉ? እናቴ ከውኃ ጉድጓድ አጠገብ ቁጭ እንዳለች፣ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ አናገራት:: መልአኩም በስሟ ጠራት!

መልአኩም፣ «አጋር፣» አላትና፣ «ወደ እመቤትሽ ወደ ሦራ ተመለሽና ታረቂ:: ወንድ ልጅ ትወልጂያለሽ:: ስሙንም እስማኤል ትዪዋለሽ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በኃዘንሽ ጊዜ ሰምቶሻልና:: እስማኤልም ጦረኛና ነፃ ሆኖ ይኖራል:: ዘሩም ለመቁጠር የማይቻል ይሆናል::»

ከዚያም እስማኤል ቀስቱንና በከረጢቱ ውስጥ ያጨቃቸውን ፍላጻዎች በእጁ መታ፣ መታ አደረገና፣ ዳክዬዎቹንና ወፎቹን በጭንቅላቱ ዙሪያ አሽከረከራቸው:: «ስለ እኔ እግዚአብሔር ለእናቴ ነግሮአታል:: ስለዚህ የሚያስጨንቀኝ ነገር የለም:: መጨነቅ አለብኝ? እናቴም ስለ እኔ የወደፊት ሁኔታ በብዛት የምትናገረው ለዚህ ነው:: አዩ ወይዘሮ ጂ?» አለኝ::



«አዎ፣ ገባኝ፣» አልኩ፡፡ «እስቲ ንገረኝ፣ እነዚህ የበግና የፍየል መንጋዎች፣ አህዮችና የቀንድ ከብቶች እንዲሁም ደግሞም እነዚህ ድንኳኖችና ሰዎች ሁሉ የአብርሃም ናቸው?»

«አዎን፣ ሁሉም የአብርሃም ናቸው» አለ እስማኤል፡፡

በፍጥነትም፣ «አንድ ቀን ሁሉም የእኔ ይሆናሉ!» አለ፡፡

በድንኳኖቹ መካከል አድርገን ስንሄድ፣ እኩዮቹ የሆኑ ልጆች ወደ እርሱ መጡ፡፡ «እስማኤል፣ ቀስቶችህን ሠርቼልሃለሁ፡፡»

ትንንሽ ልጆችም የወፎች እንቁላሎችንና የያዙዋቸውን ወፎች፣ እንዲሁም ወፎቹ የሚመገቡዋቸው እንሽላሊቶችንና ትሎችን እንዲሁም ለከብቶቹ ምግብ አመጡለት፡፡

«ታዲያስ፣ ስምዖን፡፡ አሁን ሄደህ በረቶቼን ልታጸዳ ትችላለህ፡፡»

እስማኤል ልጆቹ የሰጡትን ነገር ሁሉ



አልተሸከመም፡፡ ይልቁንም፣ ሁሉንም ወስደው የት የት እንደሚያስቀምጧቸው ነገራቸው፡፡

እኔም፣ «እነዚህ ልጆች ይህን ሁሉ የሚያደርጉልህ ስለ አንተ ብዙ ስለሚያስቡ ሳይሆን አይቀርም፣» አልኩት፡፡

«እነርሱ ስለሚያስቡት ነገር እኔ ግድ የለኝም፡፡ አባቶቻቸው የአባቴ አገልጋዮች ናቸው፡፡ የእነርሱ ደስታ ያዘዝኳቸውን ማድረግ ነው፡፡ አለበለዚያ ግን . . .!»

«አዎ፣ እንደምትራራላቸው ተስፋ አደርጋለሁ፡፡» አልኩት

«እ . . . እንደ ሁኔታው ነው» አለ፡፡


«ያለበለዚያማ፣ ብድሩን ታገኛለህ፡፡»

«ምንም ሊደርስብኝ አይችልም፡፡ አባቴ ማን እንደ ሆነ አያውቁም? ጌታው አብርሃም እኮ ነው!»

«በአብርሃም ቤት ውስጥ እጅግ ብዙ የሚኖሩ ሰዎች አሉ፣» ብዬ ተገረምኩ፡፡

«ትክክል! አንድ ጊዜ አባቴ ሎጥን ከጠላት እጅ ለማዳን ከሦስት መቶ በላይ ሰዎች ያሉት የጦር ሠራዊት አደራጅቶ ነበር፡፡ በወቅቱ አራት የሚሆኑ ንጉሦች አጐቴ ሎጥ የሚኖርበትን ከተማ ሰዶምና ገሞራን አጥቅተው ነበር፡፡ ከዚያም ሎጥንና ሌሎች ሰዎችን ማርከው እስረኛ አደረጓቸው፡፡ በከተሞቹ ውስጥ ያገኙዋቸውን ሀብትና ንብረት ሁሉ ይዘው ሄዱ፡፡ አባቴ ግን እነዚህን አራት ነገሥታት ወይም ሠራዊቶቻቸውን

አልፈራም! ስለዚህ አባቴ ሠራዊቱን እየመራ፣ አራቱን ነገሥታት ከሠራዊቶቻቸው ጋር ከደማስቆ ባሻገር እስከ ሖባ ድረስ አባረራቸው::






የአባቴ ሠራዊት ጨርሶ ካሸነፈ በኋላ፣ አጐቴን ሎጥንና ሌሎችንም ነፃ አወጣ::



«የሰዶም ንጉሥ አባቴን በጣም አመስግኖ ከአራቱ ነገሥታት የማረከውን ሀብትና ንብረት ሁሉ ለራሱ እንዲወስድ ነገረው:: አባቴ ግን አንድም ነገር ከእርሱ አልወሰደም! ይልቅስ ከማረከው ነገር ሁሉ አንድ አሥረኛውን ወደ ቤቱ ሲመለስ በመንገድ ላይ ለተቀበለው ካህን በስጦታ አበረከተለት:: ይህ ካህን (ንጉሥም ነበር) በጣም አስፈላጊ ሰው ሲሆን፣ ስሙም መልከ ጼዴቅ ነበር:: አሁን አባቴ የዚህ ካህን ወዳጅ ነው፤ ስለ ሃይማኖት ይወያያሉ::

«ስለ አዲሱ ሃይማኖታችን ያውቃሉ? አባቴ ከእግዚአብሔር ጋር እየተመካከረ እየሠራ ነው፤ ከእርሱ ዘንድ መልእክቶችን ያገኛል:: በብዙ አማልክት ፈንታ፣ አንድ አምላክ ብቻ፤ ካሁን ወዲያ ጣዖታት አይኖሩም:: ማንም ሰው ጣዖታትን ቢከተል አባቴ ይቆጣል::

«አያቴ ብዙ የጣዖት አማልክት ስለ ነበሩት እነርሱን

ያመልክ ነበር ይላሉ:: ስሙም ታራ ይባል ነበር:: አባቴ ግን እውነተኛውን አንድ አምላክ ለመከተል በጣም ይሞክራል:: እናም እርሱ የሚያመልከውን ይህን እውነተኛ አንድ አምላክ እንድናመልክ ያስተምረናል::

«አሁን አጐቴ ሎጥም ከጣዖት አምልኮ የተላቀቀ ቢሆንም፣ አባቴ ግን ስለ እርሱ በጣም ይጨነቃል:: በሰዶም ውስጥ ወደሚደረጉ ክፉ ሥራዎች ሁሉ እየተሳበ መሆኑን ይናገራል:: ቤተሰቡ ደግሞ መጥፎዎች ናቸው:: እኔ ስሰማ ቤተሰቡ አሰቃቂ እንደ ሆነ ነው:: አባቴ ወደዚያ ስፍራ እንድሄድ አይፈቅድልኝም::

«አንድ አምላክ የሚመለክበትን ሃይማኖታችንን እወደዋለሁ:: እርሱም የሚወድሽና የሚንከባከብሽ አምላክ ነው:: እንደሚመስለኝ አጐቴ ሎጥ ጥሩውን ነገር ካየ በኋላ ወደ መጥፎ ነገሮች መሄዱ የሞኝነት ሥራ ነው:: ለዚህ ሁሉ ግን፣ ሚስቱ ምክንያት ሳትሆን አትቀርም:: በግብዣዎችና በራሷ ነገሮች የተጠመደች ሲሆን፣ ልጆችዋንም ያሳደገቻቸው በዚህ ሁኔታ ነው:: እዚህ አባቴ እንደሆነው ሁሉ አጐቴ ሎጥ በዚያ ስፍራ አለቃ አይደለም:: አባቴን የሚያስጨንቀው ብቸኛው ነገር፣ የአሮጊቷ የሦራና የእናቴ ነገር ነው::

«ሆኖም ግን፣ ሃይማኖታችን በጣም ጥሩ ነው:: አምላካችንን መፍራት አይጠበቅብንም:: አንዳንድ ሰዎች አምላካቸውን በጣም ይፈራሉ:: አማልክቶቻቸው



እንዳይቆጡ የገዛ ልጆቻቸውን መሥዋዕት አድርገው እስከ ማቅረብ ይደርሳሉ:: እስቲ አስቡት! አማልክቶቻቸውን ላለማስቆጣት፣ የገዛ ልጆቻቸውን መሠዋት:: እስቲ አስቡት! ልጆችዎን መሥዋዕት ማድረግ! አማልክታቸው ቢቆጣ፣ በአንድ ቤተሰብ ላይ ምን የከፋ አደጋ ይደርሳል? ኡህ፣ አምላካችን እንደዚህ ባለመሆኑ ደስ ይለኛል:: ይሄኔ እኔ ራሴ መሥዋዕት እሆን ነበር፣» አለና እስማኤል ተንቀጠቀጠ::

«እስማኤል ፈላስፋ ነህ:: አካባቢውን አዘዋውረህ ስለ አሳየኸኝ አመሰግንሃለሁ:: አሁን ግን መሄድ አለብን፣» አልኩት::

«ወይዘሮ ጂ. በሚቀጥለው ጊዜ ሲመጡ ፍላጻ ለቀቁ አላስደነግጥዎትም፣» አለኝ::

## 3

# አብርሃም፣ የእግዚአብሔር ፈር ቀዳጅ



«ልዕልት ሦራ፣ እባክሽን ወደዚህ ወደ መምሬ ሜዳ በሚገኝ ሰፈ ግቢ ለመኖር ከመምጣትሽ በፊት ስለነበረው ጊዜ አጫውችኝ!»

ከዚህ በፊት እንዳደረግኩት ሁሉ የመጣሁት በልዕልት ሦራ ድንኳን በር ፊት ለፊት ባለው ዝግባ ዛፍ ሥር ለመቀመጥ ነበር፡፡ ደርሼም በዛፉ ሥር ለሁለት ደቂቃ እንኳን ሳልቀመጥ፣ ልዕልት ሦራ ብቅ ብላ ወደ ውስጥ አስገባችኝ፡፡

ወዲያውም ፈገግ አለችና፣ «ዛሬ እንደምትመጪ ገምቼ ነበርና ስጠብቅሽ ነበር አለችኝ፡፡ ስለዚህም



ለጥንቃቄ ቀደም ብዬ፣ አጋር ፍራፍሬ እንድትለቅም ወደ መስክ ልኬአታለሁ፡፡ የሚጠይቁኝ ሰዎች በሚመጡበት ጊዜ ሁሉ ሁሌ ተደብቃ ወሬ ማዳመጧን መታገሥ አልቻልኩም፡፡ አዎን፣ ስፈልግሽ ነበር፡፡»

ፈገግታዋ ደብዘዝ አለና፡፡ «ባለፈው ጊዜ በዚህ አካባቢ እንደ ነበርሽ ሰማሁ፡፡ የዚያን ቀን ባለመምጣትሽ አመሰግንሻለሁ፡፡ የዚያን ዕለት እዚህ የነበረው ሁኔታ በጣም መጥፎ ነበር፡፡ የዚያች የአጋር ነገር እያንገፈገፈኝ ነው! ምን ነው ባይኔ ባላየኋት ኖሮ፡፡»

«የዚያን ዕለት በመጣሽ ጊዜ ከልጆቹ ጋር ጉብኝት ማድረግሽን፣ መሪያቸውም እስማኤል እንደ ነበር ሰምቻለሁ፡፡ በዚያን ጊዜም መቼም የማይረባ ታሪክ ሲተርክልሽ የዋለ ይመስለኛል፡፡ በዚህ ያለው ነገር ሁሉ የእርሱ እንደ ሆነ አድርጐ ጉራ ይነዛል፡፡ ለነገሩ ልክ ነው፡፡ እንደነገረሽም እገምታለሁ፡፡ የዚህ ሁሉ ነገር መጨረሻው ምን እንደሚሆን ግን አላውቅም፡፡»

«ልዕልት ሦራ የማይረባ ታሪክ ያልሽው ነገር አልገባኝም፣» አልኳት፡፡ «ዶሮዎችንና በሬዎችን ደግሞም ልዩ ልዩ እንስሳትን ሳይቀር አይቻለሁ፡፡ እስማኤል ያስፈነጠረው የቀስት ፍላጻ በጆሮዬ በኩል እያፏጨ ሲያልፍ፣ ከዚያ ተርፌ ለማውራት መብቃቴም ተአምር ነው፣» አልኩና ሳቅሁ፡፡

«ለመሆኑ ምን ነገረሽ?»

«በእርሱ ዕድሜ ያለ ልጅ  የሚናገረውን ሁሉ ነው ያወራልኝ፣» አልኩ፡፡   «ስለ እንስሳቱ ነገረኝ፡፡ እዚህ በሚኖሩ ልጆች ላይ አለቃ ነው፤ የበላይነትም አለው፡፡ አይደለም እንዴ? እንዲያገለግሉት ያደርጋቸዋል፡፡»

«ምን ምን ነገረሽ?»

«ምን ነበር? አዎ፣ ስለ እናቱ እና ስለ. . .»

«እናቱ ከቤት ወጥታ ስለ መኮብለልዋ ነግሮሻል? አስቸጋሪ ሰው ናት፡፡ ያን ጊዜ ስትሄድ እንደማትመለስ ተስፋ አድርጌ ነበር፡፡   የሚገርመው ግን፣ ከፈጠራ ታሪክ ጋር ተመልሳ መምጣቷ ነው፡፡  'ለአብርሃም ልጅ ልወልድለት ነው አለች፡፡ እንዲያውም ስሙ ማን ተብሎ እንደሚጠራ እንኳ አውቃለሁ፤፣ እግዚአብሔር ነግሮኛ ል፡፡ እግዚአብሔር አነጋግሮኛል አለች!'


«ምን ነው?» ስላት፣ «እውነቴን ነው፣ እግዚአብሔር፣ 'አጋር የሦራ አገልጋይ ተመልሰሽ ሂጂ. . .' አለኝ» አለች፡፡

«'ይኸውልሽ! ዋጋሽ ይህ ነው፣ ያው እግዚአብሔር መልሶ እዚያው ስፍራሽ ላይ አስቀመጠሽ አልኳት፡፡ «አጋር የሦራ አገልጋይ፡፡» ቦታሽን እወቂ! እንዳትረሺው!' እርሷ ግን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ራሷን ከፍ ከፍ ታደርግ ጀመር፡፡ የእኔ እኅት፣ እስማኤል የነገረሽን ሁሉ አትመኚ!»



«የተከበርሽ ልዕልት ሦራ፣ የእኔ ነገር አያስጨንቅሽ! ልክ እንደ ጓደኛሽ አድርገሽ አስቢኝ፡፡ እኔ በማንኛችሁም ላይ ለመፍረድ አልመጣሁም፡፡»

ነገሩ ሁሉ ስለ አጋርና እስማኤል፣ ተመልሶም ስለ እስማኤል- ከዚያም ስለ አጋር በመሆኑ፣ ዛሬም ልዕልት ሦራ የመጣሁበትን ታሪክ መተረክ እንደማትጀምር ተረዳሁ፡፡



በመጨረሻም እንዲህ አልኳት፣ «ልዕልት ሦራ እኔ በመጣሁበት አካባቢ አስገራሚ ታሪኮች ይነገራሉ፡፡ በነበርሽበት ከተማ በዑር አስደናቂ ነገሮችን ቆፍረው እያወጡ ነው፡፡ ስለ ባለቤትሽ ስለ አብርሃም ብዙ ዓይነት አስገራሚ ታሪኮች ይነገራሉ፤ እነዚህ ታሪኮች ምናልባትም አፈ ታሪክ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በጣም ጥሩ! አሁን ልዕልት ሦራ ለነገሩ ትኩረት

መስጠት ጀመረች::

«ስለ አብርሃም? ታሪኮች?» አለች::

«አዎ» አልኳት:: ታሪኮቹ ሁላችሁም ለመኖር ወደዚህ ከመምጣታችሁ በፊት አብርሃም በዑር ይኖር ስለ ነበረበት ጊዜ ነው የሚያወሱት::»

«ወደ ከነዓን መጥተን መኖር ከጀመርን አሁን ከሃያ ዓመታት በላይ ሆኖናል:: በካራን ለብዙ ዓመታት ኖረናል:: በዑርማ ከኖርን ረጅም ጊዜ ነው» አለች ልዕልት ሦራ:: «ታዲያ ታሪኮቹ ስለ ምን ነበሩ?»

«ታሪኮቹማ፣ ታራ የአባቶቹን እምነት እንደ ተወ፣ ከዚያም ወደ ጣዖት ፊቱን እንደ መለሰ፣ የጣዖት ምስሎችንም እየሠራ እንደሚሸጥ፣ አብርሃምንም የጨረቃ አምላክ ካህን እንዲሆንለት እንዳስተማረው ነው:: እንዲሁም አብርሃም በጣዖት ምስሎች ባለማመኑ፣ አንድ ቀን ተነሥቶ በሱቅ ውስጥ ሞልተው የነበሩትን የጣዖት ምስሎች እንደ ሰባበረ፣ በዚህም ይሞት ዘንድ እንደ ተፈረደበት ነው:: እንደሚሉትም ያመለጠው በተአምር ነበር:: ታራ ግን፣ «ልጄ ከዚህ ከዑር መውጣት አለብን» ብሎት ነበር::





ይሄኔ ልዕልት ሦራ፣ «ይህን ሁሉ ታሪክ ከየት ነው የሰማሽው? ከቅዱስ መጽሐፍሽ ውስጥ አንብበሽው ነው?» አለችኝ::

እኔም፣ «አይደለም» አልኳት::

«ጥሩ» አለችና፣ «ቅዱስ መጽሐፍሽ ውስጥ የምታነቢውን አጥብቀሽ መያዝ አለብሽ:: መጽሐፍ ቅዱስ' ነው የምትሉት?

«አዎ፣» አልኳት::

«ስለዚያ ጊዜ ማውራት ትተን ነበር፣» ስትል ልዕልት ሦራ ቀጠለች:: «የጨረቃ አምላክና ጣዖታትን ማምለክ ትተናል:: እግዚአብሔር ባለቤቴን ጠርቶ አናገረው:: ስለዚህ ነገር ቀደም ሲል አልነገርኩሽም ነበር?»

«አዎ፤ ጥቂት ነግረሽኝ ነበር» አልኳት::

ስለ ዑር የሠለጠኑ ነዋሪዎች፣ ስለ ሳይንሳቸው፣ ስለ ሕጕቻቸው፣ ስለ ግሩም ሕንፃዎቻቸውና ስለ ሥልጣኔ አኗኗራቸው ካነበብኩት ልጠይቃት ፈልጌ ነበር:: ግን ነገሩ እንዳልጣማት አስተዋልሁ:: ስለ ጨረቃ አምላክ መናገር እንዴት ትጠላ ነበር! በተጨማሪም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዳተኩር ነግራኛለች:: አሁን አሁን ትንሽ እየፈራኋት መጥቻለሁ::

ቢሆንም ራሴን አበረታታሁና የተቀመጥንበትን ድንኳን ዞር ዞር ብዬ ተመልክቼ፣ «ልዕልት ሦራ ትተሽ የመጣሽው ነገር አይናፍቅሽም?» አልኳት::


«ስለ እነዚያ ነገሮች ዳግም አንነጋገርም!» አለችኝ ልዕልት ሦራ ቆጣ ብላ:: «ስለ ነበርንባቸው ምቾቶች ወደ ኋላ ተመልሼ በማንሣት ወደ ፈተና መግባት አልፈልግም:: ስለዚህ በዑር የነበረንን ምቾትና አብሮትም የነበረውን ክፉ ነገር ሁሉ እዚህ ላይ መርሳቱ መልካም ነው:: ዳግም ወደ ኋላ መመልከት ጨርሶ አይኖርም! ወደ ኋላ በምመለከትበትና በማስታወስበት ጊዜ አእምሮዬ ሚዛናዊ የሆነ ፍርድ ሊኖረው አይችልም:: የአንቺም ቢሆን ሊኖረው አይችልም፣ ስላለፈው ምቾት በምንናገርበት ጊዜ ስለ ነበረው ክብር እናጋንንና፣ ከነበረው ምቾት ጋር የነበረውን አስከፊ ነገር ሁሉ እንዘነጋለን:: ወደ ኋላ መመልከት በፍጹም አይኖርም! መፈክራችን:- «ወደፊት!» የሚል ነው::

«ልዕልት ሦራ ስለ ጠቃሚ ምክርሽ አመሰግናለሁ፣»



አልኳት::

ከዚያም ልዕልት ሦራ ቀጠለችና፣ «የምችለውን አጫውትሻለሁ፣» አለችና፣ «ከዑር ተነሥተን ስንጓዝ ወደ ሰሜንና ምዕራብ እስከ ካራን ድረስ ተጓዝን:: ብዙ ነበርን፤ እንስሳቱም በርካታ ነበሩ::





«ካራን ታላቅ የንግድ ከተማ ነች:: የፐርሺያና የሕንድ ነጋዴዎች ለንግድ ወደዚህች ከተማ ይመጡ ነበር:: በአንዳንድ ሁኔታዋ ካራን ከዑር ጋር ትመሳሰል ነበር:: ዘመናዊ ምቾቶችዋና የጨረቃ ጣዖት ማዕከል መሆንዋም ያመሳስላት ነበር:: ጉዞአችንን ብዙም አልቀጠልንም:: አባታችን ታራ ጉዞአችንን እንድናቋርጥ አዘዘን:: ጥቂት እንኳ እልፍ ማለት አልፈለገም!!»

ይህ ታራ ቋሚ የጣዖት አምላኪ ነበር ብዬ አሰብኩ:: መጀመሪያ ራሱ ጣዖታትን ያመልክ ነበር:: ከዚያም

ልጆቹን አብራምን፣ ናኮርንና ሐራን (ካለ ዕድሜው የሞተውን የሎጥን አባት) ለእነዚህ ጣዖታት እንዲሰግዱ አድርጐ አሳደጋቸው:: አንዴ ከዑር ከወጣ በኋላ በሌላ ከተማ በኃይል ተቀምጦ ነበር:: ምናልባት በካራን ይህን ያህል አልተሳበም ይሆናል ብዬ አሰብኩ:: ነገር ግን፣ ማንም ሰው እንዳይጓዝ አድርጐ ነበር::

ልዕልት ሦራ ቀጠለችና፣ «በካራን አራታችን ማለትም አባታችን ታራ፣ አብርሃም፣ የወንድማችን ልጅ የሆነው ሎጥ እና እኔ ነበርን:: ሎጥ አባቱ ከሞተ በኋላ እኛ ያሳደግነው ልጅ ነው:: በካራን መኖር ስንጀምር ሥራችን ከብቶች ማርባት ነበር:: ለዚህም ሥራ ብዙ አገልጋዮች አስፈለጉን:: ባለቤቴ ብዙ ጊዜውን ያሳልፍ የነበረው ስለ አንዱ እውነተኛ አምላክ በማሰብ ነበር:: እግዚአብሔርም ለአብርሃም እየተገለጠለት መጣ::



«መጨረሻም ታራ ሞተ:: ከዚያም አንድ ቀን እግዚአብሔር ባለቤቴን በካራን ሳለ ተናገረው:: እርሱም የሚወደውንና የቅርብ የሆነውን ነገር ሁሉ እንዲተው ነገረው:: 'ወደ ማሳይህ ስፍራ ሂድ' አለው:: ከዚያም እግዚአብሔር የአብርሃም



ልጆች ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ ተስፋ ሰጠው:: 'በአንተ የዓለም ሕዝቦች ይባረካሉ' አለው:: (ይህ የመሲሑ ተስፋ ይሆን ወይ? ብዬ አሰብኩ:: ዕቅዱን አስታወሳችሁ?)

ከዚያም ልዕልት ሦራ በረጅሙ ተነፈሰችና:: «እስከ አሁንም ድረስ ወንድ ልጅ የለንም» አለች:: «ያለው ይህ እስማኤል ብቻ ነው:: በዚያን ጊዜ እስማኤል አልተወለደም ነበር::»

እንደገና ስለ እስማኤል የሚወራ መሰሎኝ ነበር::

«እባክሽን ከካራን ስትወጡ ስለሆነው ነገር ጨምረሽ ንገሪኝ፣ ልዕልት ሦራ» አልኳት::

«በዚያን ጊዜ ብዙ ነበርን:: ባለቤቴም፣ 'ካሁን ወዲያ ሙቅና ቀዝቃዛ ውኃ መታጠቢያ ያላቸው የሚመቹ ቤቶች፣ ምንም ዓይነት የቅንጦት ነገሮች አይኖረንም:: የዛሬው ጉዞአችን እግዚአብሔርን የመከተል ጉዞ ነው:: ከአሁን ጀምሮ ኑሮአችን በድንኳኖች ውስጥ ይሆናል::' ሲል አስጠነቀቀን::



ሁሉም ሰው «ወደ የት ይሆን የምንሄደው?» የሚለው ጥያቄ እንዲመለስለት ይፈልግ ነበር::

«እግዚአብሔር ገና አልነገረኝም:: እኛ ዕቃዎቻችን ጭነን መሄድ ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ይመራናል::»

«በየትኛው መንገድ ነው የምንሄደው?» ሲሉ ሁሉም ጠየቁ::

«የምንሄደው ከመጣንበት ተቃራኒ በሆነ አቅጣጫ ነው፣» አለና አብርሃም ነገራቸው::

«ከዚህ በስተ ሰሜን ወዳለው እስከ ሴኬም ድረስ እግዚአብሔር መራን:: በዚያም እግዚአብሔር ባለቤቴን





በትልቁ በሞሬ ዛፍ አጠገብ እንደገና ተናገረው:: በዚያም እግዚአብሔር ምድሪቱን በሙሉ ለልጆቻችን እንደሚሰጥ ተስፋ ገባ:: ባለቤቴም በዚያ ለአንዱ እውነተኛ አምላክ መሠዊያ ሠራና እኛ ሁላችን አመለክነው::

«ከዚያም በቤቴል አቅራቢያ ወዳለው ተራራማ አገር ሄድን:: ባለቤቴ በዚያም ሌላ መሠዊያ ሠራ:: አብርሃም ቤቶች አይሠራም፤ እርሱ የሚሠራው መሠዊያዎችን ነው::»

በድጋሚ፣ የዑሩ ቀርቶ በካራን በነበረች ጊዜ የነበራት ምቾት ትዝ ይላት እንደ ሆነ ለጥቂት ልጠይቃት ነበር:: ቅድም እንደ ሆነው ሁሉ፣ መልስዋ አይሆንም እንደሚሆን አስታወስሁ:: ስለዚህም አልጠየቅኋትም::

«ይታይሽ፣» አለችኝ ልዕልትዋ፣ «ያህዌን መከተል ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉ ነገር ችግር የሌለው አልነበረም:: ስለዚህ ስሕተቶችን ፈጽመናል::»

«ስለ እነዚህ ስሕተቶች ብትነግሪኝ ቅር ይልሻል?»

ስል ጠየቅኋት?

እርሷም፣ «አይከፋኝም እነግርሻለሁ፣ እኛ በትክክለኛው አቅጣጫ እንሄዳለን ስንል ስላጋጠሙን ስሕተቶች አጫውትሻለሁ። ምናልባትም ስለ ስሕተታችን መናገር፣ ሌሎች የያህዌ ተከታዮች በተመሳሳይ ወጥመድ ውስጥ እንዳይገቡ ይረዳቸዋል። ሁላችንም ብንሆን የራሳችን ፈቃድ አለን። ስለዚህ ሁላችንም ስሕተት እንሠራለን። ግን ንስሐ ብንገባ ያህዌ ርኅሩኅ ስለሆነ ይቅር ይለናል።

«ለመሆኑ በግብፅ በነበርን ጊዜ ወደ ቤተ መንግሥት እንደ ወሰዱኝ ሰምተሻል? ወደ ቤተ መንግሥት መቅርብ ማለት ምን እንደ ሆነ ታውቂያለሽ?»

«አዎ፣አውቃለሁ፣» አልኳትና፣ «ያደግሁት በእንግሊዝ አገር ነው። ብዙ ጓደኞቼ ወደ ንግሥቲቱ ፊት በባኪንግሃም ቤተ መንግሥት ቀርበው ያውቃሉ። አንቺም የቀረብሽው ወደ ግብፅ ቤተ መንግሥት አልነበረም፣ ልዕልት ሦራ? ስለ እዚያ ሁኔታ መስማት እፈልጋለሁ» አልሁ በጉጉት።



# 4
# የልዕልት ሦራ ስሕተት

«ልዕልት ሦራ በግብፅ ቤተ መንግሥት ወደ ፈርዖን ቀርበሽ ነበር? ይህ እንዴት ሊሆን እንደ ቻለ ትነግሪኛለሽ?»

አዎ፣ እስከ አሁን ያለሁት በመምሬ ነበር። አሁንም ልዕልት ሦራ ከጥቁር የፍየል ፀጉር በተሠራው በትልቁ ድንኳን ውስጥ ሆና እያነጋገርኳት ነው። (ሳትገምቱ አልቀራችሁም!) ዛሬ አረንጓዴ ቀለም ያለው በእጅ ሥራ ያማረ ረጅም ቀሚስዋን ለብሳለች። በጣም ተስማምቷታል!

«አዎ፣ አዎ!» አለችና «በግብፅ . . . በዚያ እምነታችን ወድቆ ነበር። በዚያ ላይ ረሃብ ነበር። ረሃቡ በመጣ ጊዜ በኔጌብ እንኖር ነበር። አብርሃም፡- 'ወደ ግብፅ ካልሄድን በስተቀር መራባችን ነው። የእኔ ሦራ፣ አንቺ ውብ ሴት ነሽ' አለኝ። 'ወደ ግብፅ በምንደርስበትም

ጊዜ፣ አንዳንድ ግብፃውያን አንቺን ሊፈልጉሽ ይችላሉ፤ አንቺን ለማግኘት ሲሉ እኔን ሊገድሉኝ ይችላሉ:: ስለዚህ አንቺ እኅቱ ነኝ በይ' አለኝ::

«ለባለቤቴ ሁልጊዜ እንደምታዘዘው ሁሉ፣ በዚያን ጊዜም ታዘዝኩ:: እኅቱ ነኝ ስል እርሱም እኅቴ ናት አለ:: ማንም በዚህ አልተጠራጠረም:: ሁላችንም ግን ዋሸን፣ ድርጊቱ ጥሩ አልነበረም::»

ልዕልት ሣራ ወደ ቤተ መንግሥት የመወሰድዋ ጉዳይ በፊት እንዳሰብኩት አስደናቂና ማራኪ ነገር ሆኖ አላገኘሁትም:: እርሷም ታሪኳን የበለጠ እየተረከች ስትሄድ ነገሩ አስደናቂ ወይም የሚስብ ያለመሆኑን እየተገነዘብኩ ሄድኩ::

«ንጉሡ ለአንድ ሀብታም ነጋዴ እኅት የሚሰጠው ክብር፣ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ካሉ ቆነጃጅት ሴቶች ጋር እንድትደባለቅ ማድረግ ነበር:: እያንዳንዱ ንጉሥ የተለየ የቆነጃጅት መኖሪያ ስፍራ በግቢው ውስጥ አለው! ፈርዖን አያሌ ሴቶች በግቢው ውስጥ ቢኖሩትም፣ ግማሾቹን እንኳን በዓይኖቹ አይቷቸው





አያውቅም:: ግን በዚያ ስፍራ ይኖራሉ:: ያለው ሙዚቃ፣ ዳንስና የጥልፍ እጅ ሥራ ነው:: በተጨማሪም የሚለበሱ ጌጠኛ ልብሶችና ብዙ ዓይነት የሚበሉ ጣፋጭ ምግቦች ናቸው:: ሆኖም፣ አንዳቸው በሌላቸው ይቀናሉ:: ሴቶች ናቸው!

«የሆነ ሆኖ፣ የፈርዖን ሹማምንት በግብፅ ባዩኝ ጊዜ ለፈርዖን ስለ እኔ ሲነግሩት፣ ወደ ሴቶቹ መቆያ ቤት ወሰደኝ::

«ወይዘሮ ጂ. ሳይሽ በነገሩ የደነገጥሽ ትመስያለሽ:: የእኛም ባሕል ሆነ የግብፆች ባሕል የገባሽ አትመስይም::»


«እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አብርሃም ራሱን ለማዳን ብሎ፣ አንቺን ይህን ለመሰለ አደጋ በማጋለጡ በድጋሚ ማናገርሽ የሚገርም ነው» አልኳት ተናድጄ::

«በባለቤቴ ላይ እንዴት እንዲህ ደፍረሽ ትናገሪያለሽ፣» በማለት ልዕልት ሣራ በቁጣ መለሰችልኝ:: «ወይዘሮ ጂ. እዚህ ድረስ መጥተሽ በባሌና በእኔ መካከል ጣልቃ ለመግባት አትሞክሪ:: በሚያደርገው ነገር ሁሉ እኔ እንዳለሁበት እንድታውቂ እፈልጋለሁ:: በፍጹም አልወቅሰውም:: እኔም ሆንኩ እርሱ ብዙ ጊዜ አብረን ተሳስተናል:: ስለዚህ እርሱን ልትወቅሺው አይገባም፣» አለችኝ::

እኔም በሐፍረት ይሁን በብስጭት ክው አልኩኝ::

ከዚያም፣ «ይቅርታ አድርጊልኝ ልዕልት ሦራ፣ ስላቋረጥኩሽ አዝናለሁ፣» አልኳት::

«ታዲያ ፈርዖን እኔን ከወሰደ በኋላ፣ ለአብርሃም በጐች፣ በሬዎች፣ አህያዎች፣ ግመሎችና፣ እንዲሁም አገልጋዮችን ሰጠው::



እንዴት ወደ ተመሰቃቀለ ነገር ውስጥ ነበር የገባነው:: ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን አሁንም የራሱ ዕቅድ ነበረው:: እግዚአብሔር በፈርዖንና በቤተ ሰዎቹ ላይ ጽኑ ደዌ ላከባቸው:: የፈርዖንም አስማተኞች ይህ ደዌ የተላከባቸው በእኔ ምክንያት መሆኑን አስታወቁት:: ንጉሡም በአልጋው ላይ እንደ ሆነ አብርሃምን አስጠራው::



«ኋላም ሁሉም ነገር ይፋ ወጣ:: የአብርሃም ሚስት መሆኔ ታወቀ::

«ለምን አታለልከኝ?» አለ ምስኪኑ በሽተኛ ንጉሥ::



«እውነት ማለት ለግብፆች እጅግ በጣም የከበረ ነው::»

«እነርሱ አሕዛብ ስለ ሆኑ፣ እኔ የአብርሃም ሚስት መሆኔን ቢያውቁ ይገድሉታል ብለን ፈርተን እንደ ነበረ እውነቱን ተናግረን ወጣን::»

«እንደተናገርነው፣ ታሪካችን የሚያሳቅቅ ይመስላል:: አፈርን:: እኛ እግዚአብሔርን እናገለግላለን ከምንለው ይልቅ፣ አሕዛብ የሆኑት ከእኛ የተሻሉ መሆናቸውን አሳይተዋል:: እውነት ለመናገር፣ በግብፅ

በነበርንበት ጊዜ እግዚአብሔርን ለማገልገል ብዙም አልሞከርንም።» ይህንን ብላ ልዕልት ሦራ በረጅሙ ተነፈሰች። «ግብፃውያን ስሕተት ለመሥራት አስበው ያደረጉት ነገር የለም። ግን እኛ ስለ ዋሽን ብቻ ይህ አስፈሪ ደዌ በሁሉም ላይ መጣባቸው።

«ፈርዖን ተበሳጨ። እኔን ወደ አብርሃም ልኮ በአስቸኳይ ከአገሩ እንድንወጣ አዘዘን። ከዚያም በወታደር አሳጅቦ ወደ ከነዓን መልሶ ላከን።

«በዚህን ጊዜ አብርሃም በጣም አዘነ። ፊት ከነበረበት ድንኳኖቹን ነቅሎ ወደ ቤቴል መጣና፣ እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠየቀ።

«ግብፅ ጥሩ ያልሆነ ገጠመኝ ነበረን። አሳፋሪ ነበር።



በአንዱ እግዚአብሔር ማመንን ያስጀመረው ሰው፣ ከግብፅ ተዋርዶ ወጣ።»

«አጋርንም ያመጣናት ከግብፅ ነበር።»

«አሁንም እንደገና አነሣናት። ቢያንስ ከልዕልትዋ የአጋርን ትክክለኛ ታሪክ ገና በደንብ አላገኘሁም።



ምናልባት ጊዜው አሁን ነው።

«ይህን ጥያቄ በማንሣቴ ይቅርታ አድርጊልኝ፤ ልዕልት ሦራ፣ የአጋርን ነገር ባላነሣው እመርጥ ነበር፤ ነገር ግን ራስሽ ስላነሣሽው በመጠየቄ ይቅርታ አድርጊልኝ። ግን ለእኔም ሆነ ለአንዳንድ ጓደኞቼ ይህ ጠቃሚ ነው።

«እኔ በምኖርበት በክርስቲያን ዘመን፣ በክርስቲያኖች አካባቢ አጋር ባልሽን እንደ አሳሳተችው ይነገራል። ይህን በማለቴ ይቅርታ አድርጊልኝ!»

«አሳስታው ነው አልሽኝ? የእኔን ባል? እንዴት ተደርጐ! ሊሆን አይችልም! እርሱ ልቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ሰው ነው። እስከታገኚው ድረስ ቆዩ።»

ልዕልቷ በዚህ አባባል እንደ ደነገጠች በግልጥ ይታያል።

«አይደለም! አይደለም!» አለች በእርግጠኝነት። «ይህንን አሳብ ያቀረብኩት እኮ እኔው ራሴ ነኝ። እኔው እኮ ነኝ። አብርሃም እኮ የሚወለደውን ልጅ ለመጠበቅ ፈቃደኛ ነበር። እኔ ግን . . .

«ወይዘሮ ጂ. ትንሽ ሕፃን ለማግኘት ናፍቆቱና ፍላጐቱ ምን ያህል እንደ ሆነ ለአንቺ ላይገባሽ ይችል ይሆናል፣ ይገባሻል እንዴ?»

«ልዕልት ሦራ ላይገባኝ ይችላል። የትንሹን ወንድ

ልጃችን ልደት ይሆናል ብለን የመዘገብነው የጋብቻ ዓመታችንን ባከበርንበት ቀን ነበር:: ግን ልጅ ለማግኘት የተፈለገውን ሁሉ ለመስጠት የሚፈልጉ ጓደኞች ነበሩኝ:: ነገሩ ይገባኛል፣ ልዕልት:: እነዚህ ሰዎች በኋላ የጉዲፈቻ (ማደጐ) ልጅ ወስደው አሳደጉ:: በመጨረሻ ግን የራሳቸውን ልጅ ወለዱ:: ከዚያም ነገሮች ሁሉ ተስተካከሉላቸው::»

«ለእኔ ግን ነገሮች ሁሉ ጥሩ አይደሉም፣» አለች ልዕልትዋ:: «እኛ የማደጐ ልጅ የምንወስድበት ሁኔታ የተለየ ነው:: ይህን ልትረዺ ይገባል:: ይህን ስላልኩም አትደንግጭ:: እዚህ ባሕሉ ነው::

«አንዲት ሚስት ልጅ ካልወለደች፣ ለእርሷ ባሏ ከአገልጋይዋ ልጅ ወልዶ ሊሰጣት ይችላል::» (ይህ በክርስቲያን ዘመን ውስጥ የማይታሰብ ቢሆንም፣ ልዕልት ሦራን እንደገና ሳቋርጣት ግን አልቻልኩም::)

«ይህን የምታደርገው ሚስቲቱ ስለ ሆነች ሕፃኑ እንደ ልጅዋ ይቆጠራል:: ስለዚህ ነገሩ መልካም ስለ መሰለኝ አብርሃም ከልጃገረድ አገልጋዬ ከአጋር ልጅ እንዲወልድ አሳብ አቀረብኩለት:: ልጁም ልጄ ሆኖ ይቆጠራል:: እግዚአብሔር ልጅ ሊሰጠን የገባልን ተስፋም ይፈጸማል::

«አሳዛኝ ውሳኔ ነበር:: ምን ያህል ልቤን እንደ ሰበረው ልትገምቺ ትችያለሽ! ያን ሳደርግ ግን ትክክለኛ



ውን ነገር ያደረግሁ እንዲሁም እግዚአብሔርንም የረዳሁት መስሎኝ ነበር:: በዚያን ጊዜ ታዲያ አጋር ጥሩ ልጅ ነበረች::

ባለቤቴ ግን፣ «እግዚአብሔር የሚያደርገውን መጠበቅ አለብን:: ልጅ እንደሚሰጠን ማመን ይገባናል» ብሎኝ ነበር::

«እኔ ግን ነገሩን እንደ ሕልም ቆጠርኩትና፣ 'አብርሃም አሁን በጣም አርጅቻለሁ:: ተስፋውን እስከ ዛሬ ስጠብቅ ቆይቻለሁ:: አሁን ማድረግ ያለብህ፣ ከአገልጋያችን አጋር ወንድ ልጅ መውለድ ነው:: ያለበለዚያ አገልጋይህ ኤሊዔዘር ወራሽህ ይሆናል' አልኩት::



«ወንድ ልጅ መውለድ እጅግ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም፣ ለአብርሃም ግን እምብዛም አልጣመውም ነበር:: አየሽ የእርሱ እምነት ከእኔ ይልቅ ጠንካራ ነበር:: እኔ ግን ጨቀጨቅሁት::»

እዚህ ጋ ልዕልቲቱ እዝን አለችና አለቀሰች::

«ወይኔ ወይ ሞኝነቴ፣ሞኝ ነበርኩ ለካ! አጋር ማርገዝዋን እንዳወቀች ትዕቢተኛ ሆነች፣ ባለገች፣ ይባስ ብላ ታላግጥብኝ ጀመር::



«ከቤት ኮበለለች፤ ከዚያ ደግሞ እግዚአብሔር የታወቀ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ እንደ ነገራት በመናገር ተመልሳ መጣች::»

«ይኸውልሽ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ችግር ሆነ:: አሁን እንደምታውቂው፣ እስማኤል አሥራ ሦስት ዓመት ሆኖታል::



«በጭራሽ አላሳሳተችውም:: ታዲያ ሰዎች ቀጥለው ምን ይሉ ይሆን?»

በዚህን ጊዜ ለልዕልት ሦራ አዘንሁ:: አሁን በሐዘን ተውጣ ተቀመጠች::

«ይኸውልሽ በግብፅ ያገኘነው ይህን ነው:: በቤተ መንግሥት ተዋረድን፣ እንዲሁም ደግሞ ይህች ሴት:: ለዚህ ሁሉ ችግር እኔም ሙሉ ተጠያቂነት አለብኝ::»

«ልዕልት ሦራ፣» አልኳትና፣ «ስምሽ በመጽሐፍ ቅዱስ በክብር ዝርዝር ውስጥ ለምን እንደ ተጻፈ አሁን ይገባኝ ጀምሯል» አልኩ::

«የእኔ ስም ?»

«አዎ፣ የአንቺ ስም:: ለሴቶቻችን እንደ መልካም ምሳሌ ሆኖ ነው የተጻፈው:: የአብርሃም ድንቅ የሆንሽ ሚስቱ በመሆንሽ ነው የተጻፈው::»

«ይህ ለእኔ አይገባኝም፤ ምክንያቱም በአንድ በኩል ክፉኛ ወቅሼው ነበር እኮ፣» አለች::

«ቢሆንም፣ ልዕልት ሦራ፣ በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የመጻፍሽ ክብር የሚገባሽና የማይገባሽ መሆኑን አንቺ የምትወስኚው ነገር እኮ አይደለም፤ እርሱ ነው የወሰነው::»

ልዕልት ሦራ በነገርኳት ነገር ያለ ጥርጥር ተደስታ ነበር::

«ከግብፅ ስንመለስ ብዙ ሀብትና ንብረት ይዘን ተ መለስን። ብዙ ብርና ወርቅ ተሸክመን ነበር። ብዙ በጐችና የቀንድ ከብቶችም ነበሩን። ወደ ከነዓን የገባነው በጣም ሀብታሞች ሆነን ነበር።

«እንግዲህ ከዚያ በኋላ ነው ከሎጥ ጋር ችግር ያጋጠመን። ስለዚህ ነገር ሌላ ጊዜ እነግርሻለሁ።



5

# የሎጥ ምርጫ



«ወይዘሮ ጂ..!» አለኝ አንድ የወንድ ድምፅ ከኋላዬ።

እኔም በዚህ ተገረምኩ። ሰው ይከተለኝ ነበር እንዴ? ብዬ ደነገጥኩ።

ወዲያው ዘወር ስል፣ አንድ ሽምግል ያለ እረኛ ይሁን ሌላ ብቻ እጁን ወደ እኔ ዘረጋ።

ምናልባት ከአብርሃም እ ረኞች መካከል አንዱ ሳይሆን አይቀርም፣ ብዬ ለራሴ ተናገርሁ። ያም

ቢሆን የሚያስፈራኝ ነገር የለም፡፡ በአካባቢው እንዲህ ያሉ እረኞች ብዙ ነበሩ፡፡ ልዕልት ሦራን በመምሬ ሜዳ ላይ በተተከለው ድንኳንዋ ውስጥ ልጉበኛት በምመጣበት ጊዜ ሁሉ ጥቂት እረኞችን አይቻለሁ፡፡ ሆኖም፣ አንዳቸውም ቀርበው አነጋግረውኝ አያውቁም፣ እኔም ቀርቤ አነጋግሬአቸው አላውቅም፡፡ ብቀርባቸውም፣ እነዚህን ሰዎች ምን ብዬ እንደማነጋግራቸው ሥነ ሥርዓቱንም አላውቅም ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አብርሃምንም ገና አግኝቼ አላነጋገርኩትም፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ ግን በሩቁ አይቼዋለሁ፡፡

«ወይዘሮ ጂ.» አለኝ ሽማግሌው እረኛ፣ «ወደዚህ እንዲህ ብቻሽን መምጣትሽ ባለቤቴን አሳስቧታል፡፡ አንድ መጥፎ ነገር ሊያጋጥምሽ ይችላል ትላለች፡፡ ደግሞም ሴቶች ብቻቸውን በዚህ አካባቢ ሊሆኑ አይገባም ብላ ትናገራለች፡፡ እርግጥ ይህ ስፍራ ለሴቶች አያስተማምንም፡፡ በአሳቧ እኔም እስማማለሁ» አለ፡፡

«ኧረ እባክህን፣ ምንም እንኳን ከኋላዬ ድንገት ስታናግረኝ ደንግጬ መለስ ብልም፣ ምንም የምፈራው ነገር የለም፡፡ አንተም ሆንክ ሚስትህ ስለ እኔ ማሰባችሁ መልካም ነው» አልኩ አክዬ፡፡ «ምን ይደርስብኛል ብለህ ነው?» አልኩት በልበ -ሙሉነት፡፡

«አየሽ- ወይዘሮ ጂ.፣ በዚህ አካባቢ አንበሶችና ድቦች አሉ፡፡ እነዚህ አውሬዎች እንስሳትንም ሆነ ሰዎችን ሌ



ላም ያገኙትን ሁሉ ይበላሉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን? በዚህ አካባቢ ወንዶችም አስፈሪዎች ናቸው!»

«አ!፣ ታዲያ ምን ማድረግ አለብሽ ትለኛለህ? ስለ አብርሃም ታሪክ ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡ ታዲያ እዚህ የምመላለሰው ይህን ታሪክ ለመረዳት ነው፡፡»

«ወደ ድንኳኔ ብቅ በዪ፣ የምንነግርሽ አሳብ አለን» አለ፡፡

ለጊዜው ትንሽ ተጠራጠርኩ፡፡ ሆኖም፣ ፈጠን ብሎ ቀጠለና፣ «አይዞሽ፣ ባለቤቴ በሩቁ እንዳየችሽ ወደ እርሷ እንዳመጣሽ ልካኝ ነው፣ እስከታልፊ ቆይቼ ከኋላሽ ነው የመጣሁት፡፡ ቀስ ብዬ ከኋላሽም የተከተልኩበት ምክንያት ፊት ለፊት ወዳንቺ ስመጣ ብታዪኝ ኖሮ ፈርተሽ ወደ ኋላ ትመለሻለሽ ብዬ ነው፡፡ ልዕልት ሦራ የምትጠብቅሽ ከሆነ፣ ብዙም አናቆይሽም» አለ፡፡

እኔም «ኧረ ግድ የለም፣» አልኩትና፡፡ «ልዕልት ሦራ የምመጣበትን ጊዜ በፍጹም አታውቅም፡፡ እኔ ስችልና አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው የምመጣው፡፡ እየመጣሁም ላስቸግራት አልሻም፡፡»

«ያውልሽ እዚያ ጋ ያለው የመጨረሻው ድንኳን የእኔ ነው፡፡» ሽማግሌው እረኛ መለስ ብሎ፣ «ተመልከቺ! ባለቤቴ በር ላይ ቆማ እየጠበቀችሽ ነው» አለ፡፡

ከዚያም ወደ እረኛው ሰው ድንኳን መሄድ ጀመርን፡፡

«ልዕልትዋን ለመጐብኘት እንደምትመጪ ሁላችንም እናውቃለን። ሰውም ያወራል። ልዕልትም ደስ ይላታል» አለኝ።



«አዎ፣ ልዕልት ሦራ እንድመጣ ትፈልጋለች፣» አልኩና በነገሩ መስማማቴን ገለጽሁ። «ሐዘንተኛ ሴት ናት።»

«በፊት እኮ እንደዚህ አልነበ ረችም። እንዲህ የሆነችው አጋር ማስቸገር ከጀመረች ወዲህ ነው።»

ወደ እረኛው ሰው ድንኳን ዘንድ እንደ ደረስን ዓይናፋር የሆነች ሚስቱ በፈገግታ ተቀበለችን። ዓይናፋር ብትሆንም፣ ብርቱ አዛውንት ሴት ነበረች።

«ወይዘሮ ጂ. እንደ ልጄ ላይሽ ዕድሜዬ ይፈቅድልኛል፣» አለችኝ። «አንቺ አታውቂኚም፣ እኔ ግን በዚህ በኩል ብዙ ጊዜ ስታልፊ አይቼሻለሁ። ባየሁሽ ቁጥር ታዲያ <ይሀቺ ወጣት ሴት ችግር ሊያጋጥማት ይችላል> እያልሁ እሰጋልሽ ነበር። ስለዚህ ዛሬ ኤሎን ወዳንቺ መጥቶ ወደ ድንኳናችን ይዞሽ እንዲመጣ ላክሁት።



«እኔ ብመጣ፣ የሰፈራችን ሴቶች እንዳያሽሟጥጡኝ ፈርቼ ነው፣ ኤሎን ሂዶ እንዲያመጣሽ የላክሁት።

«ወደ ድንኳናችን እንኳን በደኅና መጣሽ። ልሂድና የምትጠጪውና የምትመገቢው ምግብ ላምጣልሽ።»

«የምጠጣው ነገር ብቻ ይበቃኛል፣ አመሰግናለሁ። የፍየል ወተት በቂ ይሆናል፣ እየወደድኩት ሄጃለሁ።»

«ድንኳኔ እንደ ልዕልት ሦራ ድንኳን ያማረና ሰፊ አይደለም፤ ከዑርና ከካራን ለቅቀን ከመጣን ወዲህ ማንኛችንም የሚገባን ምቾት ሁሉ የለንም።

«መቼም ልዕልትዋ የጨረቃ አምላክና ሌሎች ጣዖታት ይመለኩ ስለ ነበረበት ጊዜና ስለ ሌላው ነግራሽ ይሆናል። አሁን ያ ሁሉ ቀርቷል። አሁን የምናመልከው አንዱን እውነተኛ አምላክ ነው። ይህንንም አብርሃም አስተምሮናል። አብርሃም ጌታችን አስደናቂና ርኅሩኅ ሰው ነው። ልክ እንደሚነግረን አምላክ ያለ ሰው ነው።

«በአንድ በኩል ወደዚህ ስንመጣ ብዙ ነገር ትተን ወጥተን ይህን የመሰለ ቀላል ኑሮ እንኖራለን። ግን፣ እንዴት የከበረ ኑሮ መሰለሽ! ፍቅርና ሰላም የሰፈነበት ኑሮ፣ እግዚአብሔርን የማወቅ ሕይወት! ፍርሐት ወይም ከንቱ አምልኮ ወይም የናናር በቀል ጭንቀት ቀርቷል።

«ናናር ማን ነው?» ስል ጠየቅኋት።

«የጨረቃ አምላክ ነው፣ ወይዘሮ ጂ.። አንድ ነገር አስታወስኩ። በዚህ አካባቢ በምትሆኚበት ጊዜ እንደ ወንድ መልበስ አለብሽ። ይህን ካደረግሽ አደጋ አይደርስብሽም። እዚህ ሴቶች ግምት አይሰጣቸውም።

«በእውነት?» አልኳት።

«አየሽ፣ ሴቶችን ባሎቻቸው በሚገባ ከያዟቸው በዚያ ደስ ይሰኛሉ። ባሎቻችን ለእኛ ደጐችና ርኅሩኆች እንዲሆኑልን አብርሃም ያስተምራቸዋል። አምላኩ እንዲህ ያለ ርኅሩኅ አምላክ ነው። የአብርሃምም ባሕሪ እንደዚሁ እንደ አምላኩ ነው። ባለቤቴ ኤሎን ከሌላ ጌታ ጋር አልኖረም። ዕድሜ ልኩን የኖረው ከአብርሃም ጋር ነው።

«ስለዚህ ወይዘሮ ጂ. አለባበስሽ እንደ ወንድ ይሁን። ያኔ ከችግር ትድኛለሽ። ደግሞም ትከበሪያለሽ። እስማኤል ደፍሮ በወንድ አጠገብ የቀስት ፍላጻ አያስፈነጥርም።»

«ስለዚህ ነገር እንዴት ልትሰሚ ቻልሽ?» አልኳት።

«ኦ! አዳ በዚህ አካባቢ የሚደረገው አብዛኛው ነገር አያመልጣትም፣ ታውቀዋለች» አለ ኤሎን ምንም ያህል ሳይኩራራ።

«እንደ ወንድ ለብሰሽ በኬብሮን ገበያ ውስጥ እንደ ልብሽ መሄድ ትችያለሽ። ገበያው ከግብፅና ከ . . . የሚመጡ ብዙ ዓይነት ነገሮች አሉት።»



«ዛሬ አየሩ ሞቃት ስለሆነ ወደ ኬብሮን ገበያ የምሄድ አይመስለኝም። ይልቅስ ድንኳኑ ውስጥ ልቀመጥና ስለ አንዳንድ ነገሮች አጫውቱኝ። ይህን በመሰለ ሞቃት ቀን በድንኳናችሁ ውስጥ የሚነፍሰው አየር፣ ድንኳናችሁን ቀዝቃዛና ምቹ ያደርገዋል። የማላስቸግራችሁ ከሆነ፣ እዚህ ትንሽ መቆየት እፈልጋለሁ። እናንተም አጫውቱኝ።»

አዳና ኤሎን ደስ አላቸውና። «አይ፣ ብዙ ሥራ የለንም። በዚህ ዕድሜያችን ብዙ ከባድ ሥራ አንሠራም፤ ብንሠራም ቀለል፣ ቀለል ያለውን ነው» አሉ።

«በነገራችን ላይ አዳ፣» አለ ኤሎን፣ «ዛሬ ጠዋት ሎጥ ዘንድ ወደ ኬብሮን ሄጄ ነበር። ዛሬ ምሽት ለሰዶም ባለ ሥልጣናት ግብዣ እንደሚያደርጉ ነግሮኛል። እንዲህ ካሉ ሰዎች ጋር ሎጥ እንዴት እንደ ተወዳጀ አላውቅም።

«ሰዶማውያን ክፉ ሰዎች ናቸው። የገሞራ ሰዎችም እንዲሁ የከፉ ናቸው። የሰዎች ክፋት በምድር ላይ እየበዛ በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር ትዕግሥቱ ስላለቀ የጥፋት ውኃ እንዴት እንደ ላከባቸው አብርሃም ነግሮናል። እኔ እንደሚመስለኝ በዚያን ጊዜ የነበረው ክፋት፣ ከዛሬው ከሰዶምና ገሞራ ዓለም የባሰና የተበላሸ አይመስለኝም።»

«አንድ ነገር እውነት ነው፣» አለ ኤሎን ቀጠለና፣ «ኖኅ ከጥፋት ውኃ በፊት ሕዝቡን ስለሚመጣው አደጋ ሲያስተምርና ሲሰብክ እንደ ነበረው ሎጥ ግን ለክፉዎች ሰዎች አይሰብክላቸውም:: በዚህ እርግጠኛ ነኝ:: በአንድ ጊዜ ሁለት መንገዶችን የሚከተል ሰው ባይ፣ ያ ሰው ወጣቱ ሎጥ ነው::»

«እርሱ እኮ አሁን ወጣት አይደለም ኤሎን:: ጊዜው አይታወስህም?»

«ሁኔታው ልጅ ከነበረበት ጊዜ አልተለወጠም፤ ሁልጊዜም ወጣትነት ይሰማዋል:: እናም እዩኝ እዩኝ የምትል ሚስት አግብቷል:: ታዲያ ይህቺ ሚስቱ ወደ አጐቱ አብርሃምና ወደ አክስቱ ሦራ ዘንድ ድርሽ ብላ አታውቅም::»

«ሆኖም፣ ልዕልት ሦራን ነገሩ የሚያስጨንቃት አይመስለኝም:: በጣም ከመኳኳሉ የተነሣ የትኛው የራሷ ተፈጥሮ እንደ ሆነ ለመለየት ያስቸግራል:: በጨዋታዋም ሰው ትመርጣለች::

«ልብ አድርጊ፣ ጠንካራ ሠራተኛ አይደለችም አላልኩም:: ግብዣዎችን የመሰሉ ነገሮችን ትሠራለች:: እድምተኞችዋን ለማዝናናት በጣም ትጥራለች:: ከሠራተ ኞችዋ ውስጥ በዚህ አካባቢ ዘመዶች ያላቸውን አግኝቼ አነጋግሬአለሁ:: ሲያሳዝኑ! ምስኪኖች ናቸው:: ወደ ግብዣው የሚመጡ በትልቅ ስፍራ የሚሠሩ ግን ጠባያቸው ክፉ የሆኑ ሰዎችን በማስተናገድ በጣም



ይደክማሉ:: ባሉበት ስፍራ ስለሚደረጉት መጥፎ ተግባራት ይናገራሉ:: የሎጥ ሁለቱ ሴቶች ልጆች በዚህ ሁኔታ ውስጥ አድገው መጨረሻቸው ምን እንደሚሆን አላውቅም:: እንደምሰማው ጥሩ ልጆች አይደሉም::»

«ተው እንጂ፣ አሁን ኤሎን !» አለች አዳ::

«እውነት ነው:: ኋላ ምን እንደሚሆኑ አላውቅም:: ሎጥም አልፎ አልፎ በልጆቹ አግባብነት የጐደለው ድርጊት ደስተኛ አለመሆኑን ያሳያል:: ይሄ ግን የሚወሰነው አብሯቸው ባለው ሰው ማንነት ላይ ነው::»

«ይህን የመሰሉ ብዙ ሰዎች አሉ፣» አልኩ::

«ሎጥ በሰዶም ውስጥ ግሩም የሆነ ቤት አለው:: በምቾት የተሞላ ነው:: አጐቱ በዑር ከነበረው ቤት በላይ የተሟላ ቤት ነው:: በዚያን ጊዜ እኔ አብርሃም ቤት ውስጥ አገልጋይ ነበርሁ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሬ እስከ አሁን ድረስ ከእርሱ ጋር ነኝ::



«እንደ እውነቱ ከቦታ ቦታ የዘላንነትን ሕይወት ለመኖር ከነበርንበት አገር የወጣነው፣

ለሃይማኖታዊ ዓላማ ነበር። ከዚያም ወዲህ የጨረቃን አምላክ በማምለክ ፈንታ እውነተኛውን አምላክ ወደ ማምለክ ሕይወት ተለወጥን። ጌታዬም በመቶዎች የሚቆጠሩ የእንስሳት መንጋዎችን ገዛ። ከዚያም እኔ የእርሱ ከብቶች እረኛ ሆንኩ!»

«ይህ ለአንተ ለውጥ ነው፣» አልኩት።

«አዎ፣ አንቺው ብለሽዋል። ስለ ከብቶች ብዙ አላውቅም ነበር። ኋላ ግን ተማርሁት።»

«ወደ ሎጥ ስንመለስ፣ አብርሃም ለእርሱ ደግ ሰው ነበር። የሚያየው እንደ ልጁ ነበር። እርሱ ግን ራሱን የሚወድ መጥፎ ልጅ ነበር። ይህን ስል ይቅርታ አድርጊልኝ ወይዘሮ ጂ.፣ ግን የምናገረውን አውቃለሁ።»

«ከግብፅ ወጥተን ወደ ከነዓን የመጣንበትን ጊዜ በፍጹም አልረሳውም። ጌታዬ በግብፅ በጣም ባለጸጋ ሆኖ ነበር። እኛም ብዙዎች ነበርን። ገጠሩን እንስሳቱ ይርመሰመሱበት ነበር። ሎጥም በልጽጐ ነበር። አጐቱ የእንስሳት መንጋም ሰጥቶት ነበር።

«ከብቶቻቸው ከመብዛታቸው የተነሣ፣ ነድተን ወደ ግጦሽና ወደ ውኃ ማጠጣት ለመውሰድ ያዳግተን ነበር። የውኃ ችግር ነበረብን። በምንኖርበት በቤቴል በቂ የውኃ ጉድጓድ አልነበረም።





«በእረኞች መካከል፣ በትንሹም በትልቁም ጭቅጭና ጥል ነበር። እኔም በዚህ ችግር ተካፋይ ነበርሁ። የእኔ ጌታ ከሁሉ በላይ ስለ ሆነ፣ የእርሱ ከብቶች አስቀድመው መጠጣት አለባቸው ባይ ነበርሁ። የሎጥ እረኞች ደግሞ ልክ እንደ እርሱ ራስ ወዳዶች ነበሩ።»

«የሸክላ ድስት የብረት ድስትን ጥቁር ነህ እንደሚለው ማለት ነው፣» ብዬ አሰብኩ።

«ከዚያም፣» አለ ኤሉን ቀጥሎ፣ «የውኃው ነገር እያደር ትልቅ ችግር ሆነ። ቤተሰቡ ሁሉ የጥሉ ተካፋይ ሆነ። አንዱ ሌላውን ይወቅስ ጀመር። ጭቅጭቅ ሲኖር ነገሮች እንዴት እንደሚሆኑ ታውቂያለሽ። አንዳንዶቹ የጥሉ መነሻ ምን እንደ ሆነ

ሳያውቁ እነርሱ ዝም ብለው ይጣላሉ!

«አብርሃም በዚህ ሁኔታ በጣም ተጨነቀ፡፡ ስለዚህ ሁኔታም አነጋገረኝ፡፡


«ከዚያም ሎጥን እንዲህ አለው፣ 'ልጄ ሎጥ ሆይ፣ ይህ ነገር ጥሩ አይደለም፡፡ ይህን የመሰለ ጭቅጭቅና ጥል በእኛ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ሲካሄድ ይህ ለአሕዛብ መጥፎ ምስክርነት ይሆናል፡፡ የምንለያይበት ጊዜ ደርሷል፡፡ ብንለያይም እንኳ ወዳጅነታችን ይቀጥላል፡፡ ሆኖም ግን፣ ከአሁን በኋላ አብረን ልንኖር አንችልም፡፡'

«ከዚያ ይህ ደግ ሰው ጌታዬ ምን አደረገ? ለዚያ ለምናምንቴ ሎጥ የት መኖር እንደሚፈልግ የመጀመሪያውን ምርጫ ሰጠው፡፡»

«ጌታህ እንዴት ያለ የሰላም ሰው ነው!» አልኩት፡፡

«አዎ፣ የሰላም ሰው ነው፡፡ ጌታዬና ሎጥ ለመናፈስ ወደ ተራራ ወጡ፡፡ የሰሙ ሰዎች እንዳጫወቱኝ፣ 'ሎጥ ዙሪያህን አሻግረህ ተመልከትና ልትኖርበት የምትፈልገውን መሬት ምረጥ አለው፡፡ አንተ ወደ ሰሜን ብትሄድ፣ እኔ ወደ ደቡብ እሄዳለሁ፡፡ ወደ ምሥራቅ ብትሄድ፣ እኔ ደግሞ፣ ወደ ምዕራብ እሄዳለሁ'» አለው፡፡





«ሎጥም አሻግሮ አየና ግራ ቀኙን ካማተረ በኋላ፣ 'አጐቴ አብርሃም፣ እጅግ በጣም አመሰግንሃለሁ፣» ካለ በኋላ፣ «ወደዚያ ወደ ለምለሙ ወደሚያምረው የዮርዳኖስ ሸለቆ እሄዳለሁ፡፡ ሣሩም ለከብቶቼ መልካም ነው፡፡ የእነዚያ ከተሞች ገጽታም ያምራል፡፡ ለመኖሪያ ውብ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከፍ ያለ ምሥጋና አቀርብልሃለሁ፣ አጐቴ' አለው፡፡

«የሎጥን ስግብግብነት ስንሰማ ሁላችንም ደነገጥን፡፡ ሎጥ ሁልጊዜ የሚፈልገው ምርጥ ምርጡን ነገር ነበር፡፡ ቢያንስ፣ «አጐቴ፣ አንተ ከእኔ ትበልጣለህ፣ ስለዚህ አስቀድመህ የወደድከውን ምረጥ!» ይላል ብለን አስበን ነበር፡፡ ግን ይህን አላደረገም፣ ያሳዝናል፡፡

«በጊዜው እኛ የያዝነውን ደረቅ መሬት አልወደድነውም ነበር፡፡ እንደ እረኝነታችን፣ የሆነው ነገር ተስፋ አስቆርጦን ነበር፡፡ ግን እስቲ ተመልከቺ፣ እግዚአብሔር ጌታዬን እንዴት አድርጐ እንደ ባረከው!

«በአሁኑ ጊዜ እርሱና ሚስቱ የሚጉድላቸው አንድ ነገር ብቻ ነው:: እርሱም የራሳቸው የሆነ ልጅ ነው:: ጌታዬ እስማኤልን ይወደዋል:: እስማኤል ግን ለየት ያለ ልጅ ነው:: ልቅ፣ ኃይለኛ እና ተንኮለኛ ልጅ ነው:: እኛ ግን እንታገሠዋለን:: ጌታችንም ይታገሠዋል:: ጌታችን በጣም ደግ ሰው ነው::»

ልሄድ ብድግ አልኩ::

«ምን ነው ልትሄጂ ነው እንዴ ወይዘሮ ጂ..?» አለችኝ አዳ::

«አዎ፣ መሄድ አለብኝ፣» አልሁ::

«ወደዚያ ወደ እናንተ ዘመን ተመልሰሽ መሄድ አለብሽ?»

«የክርስቲያን ዘመን፣» አልኩና ሣቅሁ:: «እረ እየዘገየሁ ነው፣ ቀኑም እንዳይመሽብኝ::»

«በማንኛውም ጊዜ መጥተሽ ድንገት ቢመሽብሽና ማደር ብትፈልጊና ወደ እኛ ዘንድ ብትመጪ በደስታ እንቀበልሻለን፣» አለች አዳ::



«አንቺ በጣም ደግ ሰው ነሽ፣ እኔም ብመጣ ደስ ይለኛል::»

የምመጣ አልመሰለኝም ነበር:: ግን በጣም ጥሩ ሰምች አይደሉ?

«በጣም አመሰግናለሁ፣» ብዬ ትቼአቸው ሄድሁ::



# 6

# የአብርሃም እንግዶች

በልዕልት ሦራ ፊት ለፊት በትልቁ ዛፍ ሥር ለብዙ ደቂቃዎች ተቀምጬ ነበር:: ዛሬ ደግሞ ከነጭራሹ ብቅ ብሎ የሚያየኝ ሰው አልነበረም:: እንድገባ ሊጠራኝም የመጣ ሰው አልነበረም::

ከሚንቀሳቀሱት የትልቁ ዛፍ ቅጠሎች በላይ በመምሬ መስክ በተተከለው የጥቁር ፍየል ፀጉር ድንኳን ውስጥ በሩቁ የድምፅ ጉርምርምታ ይሰማኛል::

ቆይ፣ ቆይ እስቲ! የወንድ ድምፅም ይሰማል:: ይህ ድምፅ የአብርሃም ሳይሆን አይቀርም፣ አልኩኝ ለራሴ:: ታምናላችሁ? ፍርሃት ተሰማኝ!

ወደ ወፍራሙ ዛፍ ግንድ ቶሎ ብዬ ዘወር አልኩና በዛፉ ቅጠሎች ተሸፍኜ ተደበቅሁ:: አሁንም ቢሆን ከተደበቅሁበት አጮልቄ የድንኳኑን በር ማየት እችላለሁ:: ሆኖም፣ ድምፅ ይሰማኛል:: እዚህ ሆኜ ማንም ሰው ሊያየኝ አይችልም:: በደንብ ለመደበቄ እርግጠኛ ሆንኩ:: አብርሃም ወጥቶ እስኪሄድ ድረስ እዚሁ እቆያለሁ (አብርሃም ከሆነ)፣ ከዚያ በኋላ፣ ሌላ ጊዜ ወደምቀመጥበት ስፍራ ተመልሼ ቁጭ ብዬ ልዕልት ሦራን እጠብቃታለሁ::

የሚያወሩት ነገር በደንብ አይሰማኝም:: ግን «ያቺ አጋር» የሚለውን ቃል አንዴ ብቻ ሰማሁ፣ የልዕልትዋ ኃይለኛ የቁጣ ቃል ነበር::

አዎ፣ አብርሃም ነበር! አዎ፣ በእርግጠኝነት አብርሃም ነበር:: ወደ ድንኳኑ በር ብቅ አለ:: አሁን ደግሞ በድንኳኑ በር መግቢያ ላይ ተቀምጧል:: ዛሬ ልክ እንደ ቤድዊኖች ዓይነት አለባበስ ለብሷል::

ፊቱን ደህና አድርጌ መመልከት ፈለግሁ:: እርሱ ግን በቀኝ እጁ ዓይኖቹን ከፀሐይ ጨረር ለመከለል ፊቱን ጋርዶ ነበር:: ወደ ምዕራብ ወዳለው የመሬት ገጽታ ይቃኛል:: አሁን ደግሞ ወደ ምሥራቅ ዞረ:: ቆይ እስቲ፣ ምንድን ነው የሚመለከተው?

ወዲያው ከተቀመጠበት ተነሥቶ፣ የለበሰውን ረጅም ልብስ እየሰበሰበ መሮጥ ጀመረ:: ምን መጣ? በተደበቅሁበት ዛፍ ሥር ሆኜ እርሱን መመልከት ጀመርኩ::

በሩቁ ሦስት ሰዎች ወደ ሰፊው የድንኳን ግቢ እየመጡ ነበር:: ለካ አብርሃም የሚሮጠው እነርሱን ለመቀበል ነበር::

ደረሰባቸው! አ! ወደቀ እንዴ? አልወደቀም:: ሰላምታ ሊያቀርብላቸው ነው መሰለኝ ፊታቸው መሬት ላይ ለጥ ያለው::





አሁን ሁሉም በአንድነት ወደ ድንኳኑ መጡ:: እንደገና ፈጠን ብዬ ራሴን ሸፈንሁ:: ላያቸው እንድችል ሆኜ በቁጥቋጦዎቹ ውስጥ ተደበቅሁ:: እዚህ ሆኜ እስኪሄዱ ድረስ የሚሉትን መስማት እችላለሁ:: ከሄዱ በኋላ ግን ወደ ልዕልት ሦራ ድንኳን እሄዳለሁ::

በምን ምክንያት እንደ ተደበቅሁ ግን አልገባኝም!

ሰዎቹ እየቀረቡ ሲመጡ ድምፃቸው ይሰማኝ ጀመር:: ተደላድዬ ተቀምጫለሁ:: ከእንግዲህ በቀላሉ ሰዎቹ የሚነጋገሩትን በግልጽ ላዳምጥ እችላለሁ::

አብርሃም፣ «ጌታዬ፣ ውኃ እስካመጣ ድረስ ቁጭ

ብለህ እረፍ. .» አለ። በዚያም ሦስቱ እንግዶች በትልልቆቹ ዛፎች ሥር ከዚህ በፊት ልዕልት ሦራ እስክትጠራኝ ድረስ ተቀምጬ በምጠብቃት በዚያው ስፍራ ላይ ቁጭ አሉ።

አብርሃም እየተናገረ ነበር። ፊቱን በጣም ወደድኩት። «እግሮቻችሁን ለማጠብ ውኃ ላምጣላችሁ። የምትበሉትንም ምግብ ላምጣላችሁ።» አላቸው።

«እናመሰግንሃለን፣ አምጣልን፣» አሉት።

አብርሃም በፍጥነት ወደ ድንኳኑ ተመልሶ ሄደ።

ለእኔ ሦስቱ ሰዎች ተራ ሰዎች መሰሉኝ። ምንም የተለየ ነገር እንዳላየሁባቸው ተሰማኝ። አሁን ተ ቀምጠው ስለ ነበረ፣ ፊታቸውን ለማየት አልቻ ልኩም። ሆኖም ግን፣ የሚናገሩት እያንዳንዱ ቃል ግን ይሰማኛል።

ወዲያው፣ አብርሃም በትልቅ ጆግ ውኃ ይዞ መጣ።

ከዚያም በእንግዶቹ እግሮች ላይ ማፍሰስ ጀመረ። አብርሃም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት አዛውንት ቢሆንም፣ ሰውነቱ ግን ቀልጣፋ ነበር። ሚስቱ ከእርሱ በአሥር ዓመት እንደምታንስ አውቃለሁ። እርሷ የሰማንያ ስምንት ዓመት አዛውንት ነበረች።



አብርሃም ወደ ድንኳኑ በር ገባ አለና፦

«ሦራ ፈጠን በይ፣» አላት። ከዚያም፣ «ቶሎ ብለሽ ከምርጡ ዱቄት ወስደሽ፣ ለሦስት ሰዎች የሚበቃ ቂጣ ጋግሪ። እኔ ወደ ከብቶቹ ሄጄ ጥጃ እመርጣለሁ። የምመርጠው እኔው ራሴ ነኝ። ከዚያም አንድ አገልጋይ ቶሎ አርዶና ብልት አውጥቶ፣ ጠብሶ እንዲያመጣ አደርጋለሁ።»

ይህ ሁሉ ነገር ሲደረግ እኔ እዚሁ ተቀምጬ መጠበቅ አለብኝ? ስል አሰብኩ። ሆኖም፣ አልሰለቸኝም ነበር። ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁ? እንግዶቹ ስለ ደከማቸው ባሉበት ስፍራ እንቅልፍ ወሰዳቸው። ንግግር አልነበረም። ሁሉም ነገር ፀጥ ብሎ ነበር። ስለዚህም ሳይተኙ እንዳልቀረ ገመትኩ፣ እኔም እንደ ማሸለብ አድርጎኝ ነበር።

ከዚህ በኋላ የተጠበሰ የጥጃ ሥጋ፣ ትኩስ ዳቦ ይሸተኝ ጀመር። አጮልቄ ይህን ሁሉ ስመለከት አፌን ምራቅ ሞላው። አብርሃም ምግቡን በእንግዶቹ ፊት ገበታው ላይ እያስተካከለ ያቀርባል። ቅቤና ወተ ትም ነበር።

እንግዶቹ ክብ ሠርተው ከተቀመጡ በኋላ፣ የተ ዘጋጀው ምግብ በገበታ ላይ ሆኖ በመካከላቸው ተደ ረገ። አብርሃም የሚያስፈልገውን ሁሉ እያቀረበ ቆሞ ያስተናግድ ነበር።



«እነዚህ እንግዶች የተከበሩ ሰዎች መሆን አለባቸው፣» አልኩ ለራሴ።

«አብርሃም በመቶዎች የሚቆጠሩ አገልጋዮች እያሉት፣ ራሱ እንደ አገልጋይ ቆሞ እንግዶቹን ይጋብዝና የሚፈለገውን ሁሉ ያቀርብ ነበር።»

እጅግ በጣም በነገሩ ተገረምኩ። ምናልባትም ስለ እነዚህ ሰዎች አንድ ዓይነት የተለየ ነገር ወይም ምሥጢር ይኖራል ብዬ አሰብኩ።

ከእንግዶቹ መካከል ዘለግ ያለውና ጀርባውን ለድንኳኑ ሰጥቶ የተቀመጠው ሰው፣ «አብርሃም ሚስትህ ሣራ የት አለች?» አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ። ልዕልት ሣራ፣ አንድ ነገር ለማወቅ የምትፈልግ በመሆንዋ፣ ስሟ በተጠራ ጊዜ ለማድመጥ ጆሮዋን ነቃ እንደምታደርግ ገመትኩ።



(ለመሆኑ ስሟን ማን ነገራቸው?)


«ሣራ እዚያው ድንኳን ውስጥ ነው ያለችው፣» አለና አብርሃም መለሰ።

ከዚያም እንግዳው፣ «የዛሬ ዓመት በዚሁ ጊዜ እባርካችኋለሁ። ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልዳለች፣» አለው።

የዛሬ ዓመት ለሣራ ወንድ ልጅ? በእዚህ ዕድሜዋ? ይህን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው ብዬ አሰብኩ። ትንሽም ድንጋጤ ተሰማኝ።

ልዕልት ሣራ ስለዚህ ምን ትል ይሆን?

ድምፁም ቀጠለ። «በእርሷ እድሜ ውስጥ ያለች ሴት ለመውለድ እንዴት ትችላለች ብላ ለምን ሣራ ሣቀች፣ ደግሞም ተደነቀች? ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? ጊዜው ሲደርስ እንደምባርካችሁና ሣራም ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ቃል ገብቼላችኋለሁ።»



ልዕልት ሣራም እየፈራች በድንኳኑ በኩል አጮልቃ ወጣችና «እኔ አልሳቅሁም፣» አለች።

«አይደለም ስቀሻል፣» የሚል ነበር መልሱ::

ምስኪኗ ሦራም ደነገጠች:

ወደ ድንኳንዋ ከገባች በኋላ ልትስቅ ወይም ልታለቅስ ነበር ማለት ነው ብዬ አሰብኩ:: ስሜትዋ በሣቅ ተገለጠ::

ምግብ ከተበላ በኋላ፣ የአብርሃም እንግዶች ሊሄዱ ተነሡ:: «የሚቀጥለው ቆይታቸው በሰዶም እንደ ሆነ» ተናገሩ::

አዎ፣ ቀጣዩ ቆይታ በሰዶም:: አብርሃም አብሯቸው ይራመድ ጀመር::

አብረው ጥቂት ከሄዱ በኋላ፣ የሰዎቹ መሪ ቆመና አብርሃምን አናገረው:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱ ነው ይላል::

«የማደርገውን ከአብርሃም መደበቅ የለብኝም:: አብርሃም ትልቅና ኃያል ሕዝብ ይሆናል:: የዓለም ሕዝቦች በሙሉ በአብርሃም በኩል ይባረካሉ:: አብርሃም ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ትክክልና እውነት የሆነውን ሁሉ እንዲያስተምራቸው መርጬዋለሁ::

«አብርሃም፣» አለውና፣ «የሰዶምና የገሞራ ክፋት እጅግ በጣም የከፋ መሆኑ ተሰምቶኛል:: ሥራቸው ለቅጣት ወደ እኔ እየጮኸ ነው:: የሠሩት ክፋት




ከምሰማው ጩኸት ጋር መስማማቱን ለማየት ወደዚያ መሄዴ ነው::»

ከዚያም የተቀሩት ሁለት ሰዎች ወደ ሰዶም ሄዱ::

መሪው ሳይሄድ ቀረ::

አብርሃምም በፊቱ ቆሞአል:: አብርሃም ስለ ጥፋት ውኃ እንደ አስታወሰ እና፣ «እነዚያ ከተሞች ሊጠፉ ነው፤ ምስኪኑ ሎጥም ከነቤተሰቡ እዚያው ነው» ብሎ እንደ አሰበ ገመትኩ::



በተረበሸና በሚያሳዝን የፊት ገጽታ ወደፊት ቀረብ ብሎ፣ «ጌታ ሆይ፣ ኃጢአተኛውን ከጻድቁ ጋር ታጠፋለህ? በሰዶም ሃምሣ ጻድቃን ሰዎች ብታገኝስ? ለሃምሣዎቹ ጻድቃን ብለህ ከተማዪቱን አትምርምን? ጻድቃንን ከኃጢአተኞች ሰዎች ጋር እንዴት ታጠፋለህ?

የምድር ሁሉ ዳኛ በቅን አይፈርድምን?»

አብርሃም «ለአምላኬ» የተናገረበትን ሁኔታ ወደድኩት:: በጣም ታማኝ ሰው ነበር:: በአሳብ የተ ስማሙ ይመስላሉ::

«ሃምሣ ጻድቃን በዚያ ባገኝ፣ ለእነርሱ ስል ከተ ማይቱን በሞላ እምራለሁ፣» አለ «ጌታዬ::» አብርሃምን በምሕረት ዓይኖቹ እየተመለከተ::

አብርሃምም ለደቂቃ በአሳብ ተውጦ ዝም አለ:: (በሰዶም የነበሩትን ጻድቃን በአሳቡ እየቆጠረ ይሆን?) ከዚያም፣ «እኔ ከንቱ፣ ትቢያና አመድ ሆኜ ሳለሁ ከጌታዬ ጋር ለመናገር ደፍሬአለሁ:: ለመሆኑ ከሃምሣው ጻድቃን አምስት ቢጐድሉና አርባ አምስት ሰዎች በሰዶም ቢቀሩ ከተማዪቱን ታጠፋታለህን?

«አርባ አምስት ጻድቃን ባገኝ፣ ከተማይቱን አላጠፋም፣» አለ::

እንደገና አብርሃም ፀጥ ብሎ ያስብ ጀመር:: ከዚያም፣ «ጌታዬ፣ አርባ ጻድቃን ቢገኙስ?» አለ::

«ጌታዬም ይሁን» አለና፣ «አርባ ጻድቃን ካሉ እምራታለሁ::»

አብርሃም እንደገና ዝም አለ:: (እየቆጠረ ይሆን?) የተጨነቀ ፊቱን ቀና አደረገና፣ «ጌታዬ፣ እባክህን አትቆጣ! ሠላሣ ጻድቃን ቢገኙስ?»

«ይሁን አብርሃም፣ ሠላሣ ጻድቃን ከተገኙ አላጠፋትም::»



አሁንም በድጋሚ ፀጥ ብሎ ቆየና፣ «መቼም ከጌታ ጋር ለመናገር አንዴ ደፍሬአለሁና፣ ሃያ ጻድቃን ቢኖሩስ? አለ::

«መልካም:: ሃያ ካሉ ምሕረት አደርጋለሁ::»

አብርሃም በጣም የሚያስብ ይመስል ነበር:: እኔን እንደ መሰለኝ በሰዶም ስለ ነበሩት መልካም ሰዎች ያስብ ነበር:: በዚህ ምንክያት ይመስላል በጣም የጨነቀው:: ሆኖም፣ አሥር ሰዎች ይኖራሉ:: ማለትም ሎጥና ሚስቱ፣ ሴቶች ልጆቹና ባሎቻ ቸው:: በእርግጥም አሥር ይሆናሉ:: በመጨረሻም አብርሃም ዓይኖቹን ቀና አድርጐ እንዲህ አለ፣ «ጌታዬ፣እባክህን አንድ ጊዜ ብቻ ጨምሬ ብናገር አትዘንብኝ:: አሥር ጻድቃን ቢገኙ ከተማዋን ትምራለህን?



«አዎን፣ አብርሃም:: አሥር ጻድቃን ባገኝ እንኳን ከተማውን እምራለሁ::»

አብርሃምም ባገኘው መልስ የረካ ይመስል ነበር::

«ጌታዬም» መንገዱን ሄደ:: አብርሃምም ወደ ድንኳኑ ተመለሰ::

ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላወቅሁም በሰማሁት ሁሉ በጣም ከመደነቁ የተነሣ ሰዓቱ ሲሄድ አልታወቀኝም:: ለነገሩ፣ ለመሄድ ብሞክርም ኑሮ፣ ወጥቼ መሄድ አልችልም ነበር::

ወደ ልዕልት ሦራ ሄጄ እንኳን ደስ ያለሽ ልበላት? ብዬ አሰብኩ:: ይህን ባደርግ ስታዳምጥ ነበረች ይሉኛል:: ታዲያ ምን ማድረግ አለብኝ? በዚህ ምሽት ወደ ቤቴ ተመልሼ መሄድ አልችልም:: እዚህ ቁጥቋጦ ውስጥ ብቆይ ደግሞ አንበሳ ወይም ድብ ይበላኛል:: ይህንንም አዳና ኤሉን አስጠንቅቀውኛል::

ታዲያ በማንኛውም ጊዜ ብትመጪ ደስ ይለናል ያሉትን ግብዣ ብቀበልስ? ይህ ትክክለኛ ጊዜ ነው!

ከዚያም ከቁጥቋጦ ውስጥ ወጣሁና ወደ ኤሉንና አዳ ድንኳን ሄድኩ::

«ያደረጋችሁልኝን ግብዣ ተቀብያለሁ፤ ግን ነገ




ማለዳ መሄድ አለብኝ» አልኳቸው::

እነርሱም፣ «እንኳን ደህና መጣሽ ግቢ፣ ግቢ» አሉኝና ያቺ ጨዋታዋ የሚጣፍጥና በአካባቢዋ የሚደረገውን ሁሉ ማወቅ የምትፈልግ አዛውንት ሴት አዳ፣ ወዲያውኑ እጅ የሚያስቀረጥም ምግብ አዘጋጀችልኝ::

ለአዳና ለኤሉን፣ ለረጅም ጊዜ ተቀምጠው የቆዩ የአብርሃም እንግዶች ካለሁበት ሳልወጣ እንዴት አድርገው እንዳስመሹብኝ ነገርኳቸው:: አዳ ሲመጡ አይታቸዋለች:: እኔንም አይታኝ ነበር:: ነገር ግን ተመልሼ ከግቢው ስወጣ ስላላየችኝ የት እንደ ነበርኩ ስታስብ ነበር:: ድንኳናቸው በግቢው ውስጥ መጨረሻ ላይ ይገኛል::

የልዕልት ሦራን ትልቅ ዜና ላለመናገር መጠንቀቅ ነበረብኝ:: ዜናው በጣም ያስደነቀኝ ቢሆንም፣ ምሥጢሩን አውጥቼ መናገር ግን ትክክል እንዳልነበረ አሰብኩ:: ሰዶም ችግር ላይ መሆንዋን ግን ጠቀስ አድርጌላቸዋለሁ:: ይህን እነርሱም የሚያውቁት ይመስላሉ:: አዲስ ዜናም አልነበረም::

# ሰዶም እና ገሞራ




ኤሎን ሁለቱ ሰዎች ወደ ሰዶም ሲሄዱ ተመልክቷል። «አስፈሪ ቦታ ነው» አለ ኤሎን። «በዚያ ያሉ ሰዎች፣ በኖኅ ጊዜ እንደ ነበሩት ሰዎች ክፉዎች ናቸው» አለ።

«መንገዱ ሩቅ ነው?» አልኩት።

«እዚያ ለመሄድ እንዳትሞክሪ ወይዘሮ ጂ.» ሲሉ ሁለቱም በአንድ ጊዜ ተናገሩ። «እዚያ ስለሚደረጉ ነገሮች ላንቺ ለመንገር እኔን ያሳፍረኛል። ሎጥ እንዴት—»

«ወዳጆቼ፣ ወደዚያ መሄድ አልፈልግም። እኔ የፈለግሁት፣ ሁለቱ ሰዎች ተጉዘው እዚያ ለመድረስ



ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድባቸው ለማወቅ ነበር።»

«አ፣ ያማ እንደ አካሄዳቸው! ነው ፀሐይዋ ቀዝቀዝ ስትል ፈጠን ብለው ሊሄዱ ይችላሉ። አየሽ በዚያ ተራራ ላይ ሆኜ (እየጠቆመኝ) ፀሐይ ዝቅ ዝቅ ስትል አመሻሹ ላይ ማየት እችላለሁ። «የሰዶምንና የገሞራን እንዲሁም የጨው ባሕርን ገጽታ ማየት ትችያለሽ።»

«በእውነት ቁራዎች ወደዚያ ስለሚበሩ በጣም ሩቅ እንዳልሆነ እገምታለሁ።»

«አዎ፣ በደንብ አድርገሽ ልታይው ትችያለሽ።»

«አሁን ፀሐይዋ ስትጠልቅ ተኝተን ፀሐይዋ ስትወጣ ወይም ከዚያ ቀድመን መነሣት አለብን። ግን አንቺ እንደ ፈለግሽው ማድረግ ትችያለሽ። ከደከመሽ ቶሎ ተኚ።»

ትንሽ ከሸክላ የተሠራና ጭልጭል የሚል ብርሐን ያለው በዘይት የሚበራ ክር የተደረገበት ኩራዝ አላቸው። ለእኔ በድንኳኑ ውስጥ በመጋረጃ የተከፈለ ወለሉ ላይ ስጋጃ የተነጠፈበት ትንሽ ክፍል ተሰጥቶኝ ነበር። የምተኛውም በዚሁ ወለሉ ላይ በተነጠፈው ምንጣፍ ላይ ነበር።

«ይኸውልሽ እንግዲህ፣ ሁል ጊዜ ትመጫለሽ ብዬ ስለምጠብቅ እንዲህ አድርጌ የምትተኚበትን

ክፍል አዘጋጅቼልሽ ነበር:: በእነዚህ ቀናት ውስጥ አንድ የወንድ ልብስ ያስፈልግሻል:: ይህን ልብስም አዘጋጅቼልሻለሁ::»

በጣም ሳቅሁ፣ ከዚያም «አዳ፣ አንቺን የምትመስል አክስት አለችኝ:: ታዲያ ስለ ብዙ ነገሮች ታስብ ነበር:: አሳቧም ጥሩ ነበር::»

ከዚያም ወዳጆቼን ደህና እደሩ ብዬ በወለሉ ላይ ተኛሁ:: ወዲያውኑም እንቅልፍ ወሰደኝ::



# 7

# የሁለቱ ከተሞች አስፈሪ ወግ

ያ ምንድን ነው?

በሕልሜ ነበር ወይ?

መምሬ በሚገኘው በሽማግሌው እረኛ ድንኳን ውስጥ አልጋዬ በነበረው ስጋጃ ላይ ተኝቼ ነበር:: መሬቱ ከሥሬ የሚሸሸ መሰለኝ::

ወዲያው ከተኛሁበት ተነሥቼ ቁጭ አልኩ:: ፍንዳታ! የጣጣታና! እንደ መብረቅ የሚያስተጋባ ኃይለኛ ድምፅ በሩቅ ሰማሁ! በድንኳኑ ውስጥም ብልጭታዎችን ያየሁ መሰለኝ::

ምንድን ነው እየሆነ ያለው? ለማስታወስ ሞከርኩ::

አዎ! ለካ ትናትና ከተደበቅሁበት ቁጥቋጦ ውስጥ ወጥቼ ወደ ክርስቲያን ዘመን ቤቱ መሄድ ሳልችል ቀርቼ ነበር:: ከዚያም ኤሉንና አዳ ባለፈው ጊዜ

አብሬያቸው እንድቆይ ያደርጉልኝን ግብዣ ተቀብዬ ወደዚህ መጥቻለሁ:: ስለዚህ አሁን እዚህ ነኝ::

ይኸው አሁንም እንደገና ጀመረ! የመሬቱ መንቀጥቀጥ፣ የነገሮች መናጋት በጣም ያስፈራል:: እነዚህ ሁኔታዎች በአፍሪካ እንዳጋጠመኝ ያለ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደ ሆነ ለራሴ ነገርኩት:: አሁንም የበለጠ ፍንዳታ ሆነ:: ፍንዳታ!

ምን እየተከሰተ፣ ምን እየሆነ ነው?

ይህን ጊዜ ወደ ድንኳኑ መግቢያ ሮጥኩ:: የመጀመሪያው የንጋት ብርሐን እየፈነጠቀ ነበር:: ኤሎንና አዳም ተነሥተው ነበር:: ፈርተውም ነበር::

ምንም ይሁን ምን፣ ለእኛ ቅርባችን አልነበረም:: ሁኔታው ከተራራዎች ባሻገር ራቅ ብሎ የተከሰተ ቢሆንም እንኳ፣ ብልጭታዎችን፣ በሰማይ ላይ የሚፈነዱትን ትላልቅ የእሳት ኳሶችን ማየት እችል ነበር::

አሁን በግቢው ያሉ ሌሎች ሰዎችም ተነሥተዋል:: ሕፃናት ያለቅሱ ነበር:: ትልልቅ ልጆች ደግሞ ወደ ተራራው እየሮጡ ነበር:: እናቶቻቸው ግን እንዲመለሱ ይጠሯቸዋል:: እኔም ከእነርሱ ጋር አብሬ ለመሮጥ ፈልጌ ነበር::

«አይሆንም! የወንድ ልብስ ካልለበስሽ በስተቀር፣



ወደዚያ መሄድ አትችይም፣» አለችኝ አዳ:: «እኛም ብንሄድ አንጠላም ነበር፣ ግን አዛውንቶች ስለሆንን አንችልም:: በይ እስቲ ይህን ላልብስሽ:: ልክሽ የሚሆን ይመስለኛል::»

አዳ ልብሱን ቶሎ ብላ አለበሰችኝና የፍየል ወተትና ዳቦ በእጄ ሰጠችኝ:: ከዚያም ከብዙ ሰው ጋር ሄድኩ:: እየመጣ ባለው የቀን ብርሃን ውስጥም ስሮጥ የቤድዊን ሰው እመስል ነበር:: ሁላችንም ወደ ተራራው ራስ መውጣት ጀመርን::



ማታ ኤሎን ሲናገር፣ «የጨው ባሕር በተራራው ላይ የተንጣለለ ነው» ብሎ ነበር:: የሚሰማው ፍንዳታ፣ ግምግምታ በጦርነት ውስጥ ያለ የመትረየስ ተኩስ ወይም የቦምብ ፍንዳታ ድምፅ መሰለኝ::

ወደ ተራራው ጫፍ በደረስን ጊዜ ያየነው በጣም የሚያስፈራ ትዕይንት ነበር! ከሙት

ባሕር በስተ ደቡብ የሚገኙት የሰዶምና ገሞራ ከተሞች በእሳት ተያይዘው ነበልባሉ ይንቀለቀል ነበር። የሚነቀለቀለው እሳት ባልደረሰበት የከተማው ክፍሎች የሚገኙ ቤቶች ፈርሰው ነበር።

በእውነት፣ እጅግ ኃይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ነበር።

ነዋሪዎቹ ወይ ሞተዋል ወይም ደግሞ ማምለጥ በማይችሉበት ሁኔታ በእሳቱ ተከብበዋል።

ፍንዳታው፣ የእሳቱ ነበልባል እና ሁሉም ነገር አስፈሪ ነበር። ሆኖም፣ ፈርተን አልሸሸንም። ቃጠሎው አብቅቶ ጭሱ አካባቢውን እስኪሞላና ጉሮሮአችንን እስኪከረክረን ድረስ አፋችንን ከፍተን ቆምን። ከጭሱ የተነሣ አሳለን፣ ጭስ አስተፋን። ያም ሆኖ፣ ባለንበት ቆመን ቆየን።

«ኦ፣ አምላኬ፣» የሚል ለስላሳ ድምፅ ከኋላዬ ሰማሁ፣ «ኦ፣ አምላኬ እግዚአብሔር፣ አሥር ሰዎችን አላገኘህም? አሥር እንኳ?»

ማንም ሰው ይህን ድምፅ ሥራዬ ብሎ አላዳመጠም። ለእነርሱ ምንም ትርጉም አልነበረውም።

አዎን፣ ይህን የተናገረው አብርሃም ነበር። ባንድ ጊዜ አወቅሁት። ትናንትና እግዚአብሔር በከተማይቱ




ውስጥ አሥር ጻድቃን ቢያገኝ ሰዶምን እንደሚምር ተስፋ ሰጥቶት ነበር።

«አሥር እንኳ አልተገኘም?» አለ እንደገና።

ለአጭር ጊዜ መለስ ብዬ አየሁት። እንባ ከዓይኖቹ ውስጥ ይጕርፍ ነበር። ወደ ተከሰተው ጥፋት ሲመለከት ሳለ፣ ሐዘን ገጽታውን አበላሽቶት ይታይ ነበር።

«አምላኬ፣ ሎጥ የት ነው? ሎጥ የት ደረሰ?» አለ።

«የጨው ባሕርን ተመልከቱ!» አለና አንድ ሰው በፍርሃትና በድንጋጤ ድምፅ ጮኸ።



ጨዋማና ዘይታማ የሆነው ውኃ በደቡብ ዳርቻው ላይ እየተምዘገዘገ እየተነሣ ይወድቃል። በእሳት

ተያያይዘው በሚንበለበሉት የሰዶምና የገሞራ ከተሞችና እንዲሁም በሲዲም ሸለቆ ሳይቀር ተነሥቶ እየተምዘገዘገ ይንከባለላል:: ምናልባት የመሬት መንቀጥቀጡ ባሕሩን ከሥር ቀስቅሶት ሳይሆን አይቀርም:: በዚህ በቁጡ የጨው ባሕር አካባቢ፣ ሌሎች ትንንሽ ከተሞችም ነበሩ::

ሜዳው ከእነዚህ በባሕሩ አካባቢ ከነበሩና በአጭር ጊዜ በባሕሩ ከሚዋጡ ከተሞች ወደ ተራራዎቹ ላይ በሚሸሹ ሰዎች ጠቆረ::

«አ፣ አምላኬ፣ ሎጥ የት ነው?» እያለ አብርሃም ከኋላዬ ይጸልይ ነበር:: «አምላኬ፣ አንተን እንዲከተል አድርጌው ነበር:: ክፉ ስፍራ ለመኖር ለምን መረጠ? አ፣ ለምን ጌታዬ፣ ሎጥን በእውነት አድነኸዋል:: አ፣ ጌታዬ፣» እያለቀሰ ነበር::



እስማኤል አብሮት ነበር:: «አጐቴ ሎጥ ያመለጠ ይመስለኛል፣» አለ::

አብርሃም ግን ያዳመጠው አይመስልም::



በጨው ባሕር በሰሜን ዳርቻ ኢያሪኮ አቅራቢያ ምን እንደ ደረሰ አላውቅም:: ያንን ማየት አንችልም:: ሜዳውን በሙሉ የጭስ ደመና ሸፍኖታል::

አመዱና ሽታው መጥፎ የሆነ የድኝ ጠረን በዙሪያችን ሸተተ:: አመድ በየስፍራው ነበር:: እንዲያውም አመዱ እኛን አልፎ አብርሃም ግቢ ድረስ ተበትኖ ነበር::

በዚህ አካባቢ ከሚኖሩት ሰዎች ጋር የዚህ ክስተት ስሜቱና ትዝታው ለብዙ ዓመታት አብሮአቸው ሊኖር ነው አልኩ ለራሴ:: እዚህ ያሉት ሰዎች ከየአካባቢው ተፈናቅለው የሚመጡትን ሰዎች ተቀብለው እንደሚረዱዋቸው ተስፋ አደርጋለሁ:: እኔ በበኩሌ መቼም ምንም ማድረግ አልችልም:: ይልቅስ ተመልሼ ወደ ቤቴ መሄድ ይሻለኛል::

በመጀመሪያ ግን፣ ስለሆነው ሁሉ ለኤሎንና ለአዳነግሬ ልሰናበታቸውና ላመሰግናቸው ይገባል::

አሁን ሁሉም ነገር አብቅቶአል:: በጣም አሳዛኝ ክስተት ነበር! እኔ ግን ምንም የማደርገው ነገር የለም::

በተራራው ጫፍ ላይ ሆነን ስናይ፣ አሁንም ብዙ ተመልካቾች አደጋው ወደ ተከሰተበት ስፍራ ይጐርፉ ነበር:: እኔ ግን ወደ ቤቴ መሄድ

ፈልጌአለሁ።

ወደ ቤት ስመለስ፣ አዳ ምግብ አዘጋጅታልኝ ነበር። እኔም ሁላችንም እስክንረጋጋ ድረስ በዚያ ቆየሁ።

«ወይዘሮ ጂ. የለበስሽውን ልብስ ላይሽ ላይ ብታቆዪው መልካም ነው። የራስሽን ልብስ እኔ አጣጥፈዋለሁ፣» አለችኝ አዳ።

ሰው ሁሉ ከድንኳኑ ወጥቶ በድንኳኑ አቅራቢያ በቡድን በቡድን ልክ በተራራው ላይ እንደ ነበሩት ሰ ዎች ያወራል። ሌሎቹ ደግሞ ፈጥነው መሄድ ያልቻ ሉት አሁን ወደ ተራራው ወጥተው የደረሰውን ጥፋት ለመመልከት በመሄድ ላይ ናቸው።

«ሎጥ የት ነው?» እያሉ ሰዎቹ ራሳቸውን ይነቀንቁ ነበር። «አመለጠ ወይስ?»

በተራራው ላይ የነበረ አንድ የዓይን ምስክር፣ «እኔን ብትጠይቁኝ፣ አንድም ሰው አላመለጠም» አለ።

«የታወቀ ነገር የለም፣» አለ ሌላ የዓይን ምስክር። «አስታውስ፣ እርሱ የአብርሃም ዘመድ ነው፣ አብርሃም ደግሞ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነው።»

«ያም ሆነ፣ ይህ ቢያመልጥም፣ የነበረውን ሁሉ



አጥቷል። የባሕሩ ማዕበል ብዙ ማይሎቹ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ውኃውን እያንከባለለ ይጕርፍ ነበር። ሎጥ በተአምር ከዚህ ቢያመልጥም እንኳ፣ ያለ ጥርጥር ከብቶቹና ንብረቱ ሁሉ ሳይሰምጥ አይቀርም።»

አሁን ወደ ቤቴ ጉዞ ጀመርሁ። አዳንና ባለቤ ትዋን ኤሎንን ለማስደሰት ብዬ የቤድዊንን ልብስ እንደ ለበስኩ ነኝ፤ እነርሱኑ መስያለሁ። (ልዕልት ሦራን ለማየት እንደገና እመጣለሁ። ዛሬ ግን አይደለም።)



እየተጓዝኩ ሳለ፣ አንድ ሰው ወደ እኔ አቅጣጫ መጣ። የቸኮለ ይመስል፣ ነበር። አካሄዱም ያልተለመደ ዓይነት ነበር። እጆቹን እያጠማዘዘ፣ ሰውነቱንም የሚያደርገው ሁኔታ የሚያስገርም ነበር።

እያነጋግረኝም። ሮጦም ያልፈኛል

ብዬ ነበር:: እርሱ ግን ከእኔ ጋር ለማውራት የናፈቀ ይመስል በቀጥታ ወደ እኔ መጣ::

አመዱ አሁንም እየበነነ ነበር:: እንዲሁም መጥፎ የሆነ የድኝ ሽታም ይሸታል::

ሰውየው ከፊት ለፊቴ ቆመ:: ዓይኖቹ መፍጠጥ ጀመሩ::

«በጣም ያስፈራ ነበር፣» አለ:: «ትናንት ሌሊት እዚያ ነበርኩ! ዛሬ ልሞት እችል ነበር! የሰዶም ሰው አይደለሁም:: ነገር ግን ለሥራ ጉዳይ ወደዚያ ሄጄ ነበር:: ልሞት እችል ነበር!» አለ::

«ግን እኮ አልሞትክም፣» አልኩት:: «ደህና ሆነህ አሁን እዚህ ትገኛለህ፣ ደግሞም በደህና እያነጋገርከኝ ነው:: በሕይወት በመሆንህ ምሥጋና ልታቀርብ ይገባሃል፣ እናም ረጋ በል::»

የምችለውን ያህል የሰላም ፈገግታ አሳየሁትና በድምፄ ላረጋጋው ሞከርኩ::

«እዚህ መንገዱ ዳር እንቀመጥ፣» አልኩት:: (ወንድ በመምሰሌ ደስ ብሎኛል::) «ልትነግረኝ የፈለግኸውን ንገረኝ፤ እርግጠኛ ነኝ ስትነጋገር ይቀልሃል፣ እኔም አዳምጥሃለሁ::»

ከዚያም አብረን ቁጭ አልን፣ እኔም ፊቱን ደህና አድርጌ ለመመልከት ስል ወደ እርሱ መለስ አልኩ::



«ሎጥን የምታውቀው አይመስለኝም?» አለኝ በተ ረጋጋ ድምፅ::

በአምንታ ራሴን ልነቅንቅ አልነቅንቅ አላውቅም:: እርሱም መልሴን አልጠበቀም::

«ይኸውልህ ሎጥ ትናንት ገና ከምሽቱ ላይ ሁለት እንግዶች ወደ እርሱ ቤት መጥተው ነበር:: እነዚህ እንግዶች እነማን እንደ ነበሩና ከየት እንደ መጡ አላወቅሁም፤ ግን አንድ ዓይነት ትርምስና የድምፅ ጫጫታ ተሰማ::

«የሰዶም ሰዎች የሎጥን ቤት ከብበው፣ 'በዚህ ምሽት ወደ ቤትህ የመጡ ሰዎች የት አሉ? ስለምንፈልጋቸው ወደዚህ አውጣልን!' እያሉ ደጋግመው ይጮሁ ነበር:: ይህ ሲሆን እኔም በዚያው አካባቢ ነበርሁ:: አንድ ጉዳይ ነበረኝና ጉዳዬን እንደ ፈጸምኩ ከዚያ ወዲያው ለመሄድ ወሰንኩ:: የእነዚያን ክፉ ሰዎች ጫጫታ እሰማ ነበር::

«በወቅቱ የሎጥ በር ተዘግቶ ነበር:: ሰዎቹ ግን በሩን ደጋግመው ያንኳኩ ነበር::»

ከዚያም ሎጥ በሩን ከኋላ ዘግቶ ወጣና «ወዳጆቼ፣ እንዲህ ያለ መጥፎ ተግባር አታድርጉ፣» አላቸው:: ከዚያም የፈለጉትን በሴቶች ልጆቹ ላይ መፈጸም እንደሚችሉና በእንግዶቹ ላይ ግን ምንም ነገር ማድረግ እንደሌለባቸው ነገራቸው::

የሚናረገውን ስሰማ በጣም ቀፈፈኝ:: ነገሩ አስቀያሚና አሰቃቂ ነበር!



«ከዚያም የሰዶም ሰዎች ወደ እርሱ ዞሩበት:: 'ከፊታችን ዘወር በል!' አሉት:: 'ምን ማድረግ እንዳለብን የምትነግረን አንተ ማን ነህ? ወደ ከተ ማችን መጥተህ እንድትኖር አልጠየቅንህም:: ለመሆኑ ማን ነኝ ብለህ ነው የምታስበው? አሁን ከፊታችን ዘወር በል፤ ያለበለዚያ በሰዎቹ ላይ ለመፈጸም ከፈለግነው የባሰ ባንተ ላይ እንፈጽማለን!' አሉት የሚናገሩት በሙሉ አስቀያሚ ነገር ነበር::

«በዚህን ጊዜ ሎጥን ግጥም አድርገው ይዘውት::



መዝጊያውን እስኪሰብሩት ድረስ ታገሉት:: እኔ በዚህን ጊዜ በአጠገባቸው ለማለፍ እየሞከርኩ ነበር:: በዚያን ጊዜ በሩ ተከፈተና የሎጥ እንግዶች ወጡ:: እንግዶቹ በአለባበሳቸውም ሆነ በገጽታቸው ከእኛ የተ ለዩ ነበሩ:: ከዚያም ሎጥን ጐትተው ወደ ቤት ውስጥ አስገቡትና በሩን ዘጉት:: ይሄኔ በውጪ የነበሩት ሰዎች አንዱ ሌላውን ማየት ስላልቻለ፣ እርስ በርስ በእጃቸው አንዱ ሌላውን ይዳብሰው ጀመር::

«ይኸውልህ በዚያ ስፍራ የሆነውን አየሁ:: ሁላቸውም ዓይኖቻቸውን ታወሩ!»

«በእነዚህ ሰዎች በኩል ማለፍ በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም፣ እኔ ግን አልፌ ወደ ከተማው በር በፍጠነት ሄድኩ:: የሎጥ ቤት ከከተማው በር ቅርብ ነበር:: የበር ጠባቂውም እንድወጣ ፈቀደልኝ:: በሰዶምም ሆነ በገሞራ ሌሊቱን በዚያ ማደር አልፈለግሁም ነበር:: በፍጹም ፈልጌም አላውቅም:: ለሥራ ጉዳይ ወደዚህ ከተማ በሄድኩ ቁጥር የምመለሰው ቀኑ ሳይመሽ ነበር:: መጥፎ ቦታ ነው!

«ከከተማዋ ወጥቼ አቅራቢያዋ በሚገኝ በዞዓር ወዳለው ትንሽ የእንግዶች ማደሪያ ገባሁ:: አሁን የምመጣው ከዞዓር ሸሽቼ ነው:: ምክንያቱም የጨው

ባሕር ማዕበል በመቃረብ ላይ ነበር:: አሁን በመጣደፍ ላይ ያለሁት ወደ ቤቴ ወደ ኬብሮን ለመሄድ ነው:: እኔ. . .»

«ታዲያ እኮ ወደ ኬብሮን የምትሄደው በዚህ መንገድ አይደለም:: ወደ ኋላ መመለስ አለብህ፣» አልኩት::

«አውቃለሁ፣ ይህን አሁን ተረድቻለሁ:: ያየሁት ነገር ሁሉ ራሴን ስላዞረኝ፣ ምንንም ዘንግቼው ነበር፣» አለ::

«ይህ ስለ ሎጥ ለመጨረሻ ጊዜ ያየህበት ሁኔታ ነበር?» አልኩት::

«አይደለም፣ አይደለም!» አለ:: «በከተማው አጠገብ በዞዓር በቆየሁ ጊዜ፣ ያ ሁሉ ጥፋት ከመድረሱ በፊት አስፈሪ የሆነ ሁኔታ ሰማሁ:: ከከተማው በር ውጪ ጩኸት፣ ጫጫታ፣ እሪታና ዋይታ ይሰማ ነበር:: ብቻ የሚሰማው የስቆቃ ድምፅ ነበር::

«እኔ ስመለከት፣ ሎጥንና ሁለት ሴቶች ልጆቹን አየሁ:: ዓይኖቻቸው ፈጥጠው ከቦታቸው ሊወጡ የደረሱ ይመስሉ ነበር:: እያለከለኩ ነበር::





«የከተማውን በር እንዳለፉ፣ ብልጭታዎችና ኃይለኛ ድምጾች አስተጋቡ:: በጣም አስፈሪ ነበር! ሁላችንም መሬት ላይ ተወርውረን ተረፈረፍን:: ስፍራው በሙሉ ተንቀጠቀጠ::



«ሎጥና ሴት ልጆቹ ያለቅሱ ነበር:: ሎጥ፣ 'ወየው ሚስቴ!' ወየው ምስኪኗ ሚስቴ! እያለ ይጮህ ነበር:: «ወደ ኋላ እንዳትመለከቺ፣ በምንም ዓይነት መዘግየት የለብሽም፣» ተብላ ነበር:: እርሷ ግን የተባለችውን ሳታደርግ ቀርታ ያው የጨው ሐውልት (አምድ) ሆና ቀረች:: አሁን ሞታለች!»

«ሴቶች ልጆቹም ቢሆኑ እያለቀሱ ነበር:: ልባቸው በሐዘን ተሰብሮአል:: ሊዳሩላቸው የነበሩ እጮኛዎቻቸው እዚያው እሳቱ ውስጥ ቀርተዋል:: 'ለምን ምክርን ሳያዳምጡ ቀሩ' አለች ከልጃገረዶቹ መካከል አንዷ እያለቀሰች:: 'አባታችን እግዚአብሔር ከተማዋን ሊያጠፋት እንደ ሆነ ነግሯቸው ነበር:: እነርሱ ግን ይስቁ ነበር:: እነርሱን የመሰላቸው አባታችን በድንገት በጣም መንፈሳዊ ሆኖ የተናገራቸው መሰላቸው:: እንዲያውም ቀልድ አደረጉት!'

«'ሁላችንም ብንሆን እዚያው በእሳት ተከብበን ነበር!' እያለች ታቃስት ነበር ሌላይቱ:: 'የአባታችን እንግዶች ሁላችንንም ከቤት ውስጥ ጉትተው ባያስወጡን ኖሮ፣ እንሞት ነበር:: ሁላችንም ከስፍራው እስክንወጣ ድረስ ከተማዋን እንደማያጠፉ ነግረውን ነበር::' ልጃገረዲቱ አሁንም እየተንቀጠቀጠች ነበር::

«ይህ የሆነው ዛሬ ማለዳ ነበር:: ግን በኋላ፣ የጨው ባሕር ሰዶምንና ገሞራን ሙሉ በሙሉ ከሸፈነ በኋላ ገና በኃይል እየዘለለ ወጥቶ ይወርድ ነበር:: ሁላችንም ከዞዓር ወጥተን ሸሸን::

«ለማንኛውም የእኔ ጉዞ ወደ ቤቴ ለመሄድ ነበር:: ሎጥ ወዴት እንደ ሄደ በፍጹም አላውቅም::



ምናልባት ወደ አንድ ዋሻ ሄዶ ይሆናል:: የሸሹ ሰዎች ሁሉ ወደ ዋሻ እንሄዳለን ነበር ሲሉ የነበረው::»

«አንድ ሰው ይህን ለአብርሃም መንገር አለበት፣» አልኩ::

ሰውየውም፣ «እኔ እነግረዋለሁ፣ እንዲያውም ባገኘውና ባነጋግረው ደስ ይለኛል:: በጣም ድንቅ ሰው ነው:: እርሱ እንደሚያጽናናኝና እንደሚያበረታታኝ አምናለሁ:: ስላነጋገርሽኝ አመሰግንሻለሁ:: ያየሁትንና የሰማሁትን መተንፈስ ፈልጌ ነበር:: አሁን ከቅድሙ የተሻለኝ ይመስለኛል:: በል ደህና ሁን» አለኝ::

እኔም ሄድኩ:: «ወደ ቤት መመለስ አለብኝ፣» አልኩ::

ጊዜው የተደበላለቀብኝ መሰለኝ:: ብዙ ዜና ሳዳምጥ ቆየሁ::

ከዚያም የበለጠ ሌላ ትልቅ ዜና ትዝ አለኝ:: ልዕልት ሦራ ልጅ ልትወልድ ነው!

# 8

# አብርሃም ሰፈሩን ነቅሎ ተጓዘ

ለረጅም ጊዜ የመምሬን ሜዳ ሳላይ ቆየሁ:: ሰደምና ገሞራ የጠፉበት አስፈሪው የመሬት መንቀጥቀጥ ከተከሰተ ወደ አንድ ዓመት ገደማ ይሆናል:: ከተሞቹ በእሳት ተያይዘው ይቃጠሉ በነበረ ጊዜ ሁኔታውን መምሬ አጠገብ በነበረው ተራራ ላይ ሆኜ አሻግሬ ካየሁ በኋላ፣ ተመልሼ ወደዚያ ስፍራ ለመሄድ ፈራሁ:: ቢሆንም፣ የጀመርኩትን ታሪክ መፈጸም አለብኝ::

በተጨማሪም፣ ልዕልት ሦራ በቅርቡ ልጅ ልትወልድ የመሆኑን ትልቁን ዜና ሳስብ ቢያንስ ቢያንስ ሄጀ እንኳን ደስ አለሽ ማለት እንዳለብኝ አሰብኩ::

ግን፣ ታምናላችሁ? መምሬ ሜዳ በደረስኩ ጊዜ፣ ከትልልቆቹ ዛፎች ሌላ ምንም ነገር አልነበረም:: ዛፎቹ ጥቂት የጠወለጉ ሲመስሉ፣ መሬቱ ተ



ቃጥሏል:: ድንኳኖቹ ተተክለው የነበሩበትን፣ የእንስሳቱ በረት የነበረበትን፣ እንስሳቱ ይግጡ የነበረበትን ስፍራ ሁሉ ማየት ትችላላችሁ:: ደግሞም፣ እስማኤል እንስሳቱን ሰብስቦ የነበረበት ግቢ ምልክትም አለ:: ሁሉም ነገር ግልጽ ሆኗል:: ከጥቁር ፍየል ፀጉር የተሠራው ድንኳንም የለም::



የተለያዩ አሮጌ ዕቃ ስባሪዎች፣ የሸክላ ስባሪዎች፣ የእንጨት ቁርጥራጮች፣ የተቀዳደዱ የፍየል ፀጉር ሸራዎች በየስፍራው ተጥለዋል:: ከድንኳኖቹ የወጡ ክምሮች እንዲሁም የእሳት አመድና አጥንቶች ይታያሉ:: ግን ምንም ዓይነት ድንኳን ወይም በግ ወይም ፍየል ወይም አህያ የለም:: አንድ ሰው እንኳ

አይታይም። አሁን ባዶ ሆኖ እንደሚታየው መስክ እኔም ባዶነት ተሰማኝ።

አዳ በዚያን በሰዶም ጥፋት ማለዳ፣ አንድ ልብስ አንሥታ አልብሳኝ የነበረውን ያንኑ የወንድ ልብስ ራሴን ላለማሳወቅ ለብሼ ነበር። ምክንያቱም «ወደዚህ በመጣሽ ቁጥር ልበሽው፣» ብላኝ ስለ ነበረ ነው።

በትልልቆቹ ዛፎች ሥር ተጠልዬ ሁለት ለማኞች የልዕልት ሣራ ድንኳን በነበረበት ስፍራ ዙሪያ የነበረውን ነገር ሁሉ እያገላበጡ ያገኙትን ለመውሰድ ሲሞክሩ ሳይ የአዳን ምክር በመስማቴ ደስ አለኝ።



ምናልባት የሚያውቁት ነገር ሊኖር ይችላል ብዬ ከነበርኩበት ስፍራ መጥቼ ወደ እነርሱ መጣሁና፣ «ወዴት ሄዱ?» ብዬ ጠየቅኋቸው።

«እነማን?»

«አብርሃምና ሰዎቹ። በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ነበሩ።»



«እንጃ፣ ስለ እነርሱ ማወቅ ነበረብን እንዴ?»

በጥርጣሬ ዓይን ተመለከቱኝ።

«በመሬቱ መንቀጥቀጥ ምክንያት ነው የሄዱት?» አልኩና አጥብቄ ጠየቅኋቸው።

«እነርሱን ራሳቸውን ጠይቅ።»

«የት እንዳሉ አላውቅም። እኔ እንዴት ልጠይቃቸው እችላለሁ?» አልኩኝ።

«ከዚህ ስፍራ እንደሚለቁ መልእክተኛ ወደ ዋሻችን ልከው የነገሩን አድርገህ የምትገምት አይመስለኝም። ይገባሃል?»

ሌላ ዘዴ ፈለግሁና፣ «በዋሻ ውስጥ ነው የምትኖሩት፣ አይደለም?» አልኳቸው

«አዎ። ሌላማ የት እንኖራለን? ቤቶች የሀብታሞችና ያማረባቸው ሰዎች ናቸው። እኛ ግን ሀብታሞችና ያማረብን ሰዎች አይደለንም። ምስኪኖች ነን። ድንኳኖች ደግሞ ብዙ ሥራ የሚጠይቁ ነገሮች ናቸው። ስለዚህ እኛ የምንኖረው በዋሻ ውስጥ በመጠለል፣ ትርፍራፊ በመለቃቀም ነው። ሌላ ማወቅ የምትፈልገው ነገር አለ?» ከዚያም ለማኙ በንቀት ዓይን እያየኝ ተመለሰ።

አንደኛው፣ «ወዳጄ እዚህ ምንም ነገር የለም፣» ሲል ለጓደኛው ነገረው።

«ጥፋቱ በደረሰ ጊዜ ወደ ዋሻ ከሸሹት መካከል ናችሁ?» ብዬ ጠየቅኋቸው::

«አይደለንም:: እዚሁ በዋሻ ውስጥ ተወልደን ያደግን ሰዎች ነን:: ኋላ ግን አዲስ ጐረቤቶችን አገኘ ን:: ሀብትና ንብረታቸውን ሁሉ የት ጣሉ? በአቅራቢያችን ባለ ዋሻ ውስጥ ሎጥ ጐረቤታችን ሆኖ ይገኛል::: ሁለት ሴቶች ልጆቹ ከእርሱ ዘር ለማግኘት ብለው ወይን ጠጅ ካጠጡት በኋላ ከእርሱ ልጆች ወለዱ:: አሁን ሎጥ አባታቸውም የልጆቻቸውም አያት ነው:: ይገርማል!» አሉ እያላገጡ::

«ምን ማለትህ ነው?» አልኩት:: በተናገረው አፍሬ፣ «ስለ ሎጥ ሰምቻለሁ::»

«እርግጥ ልትሰማው የሚገባ ነገር አይደለም:: የልጃገረዶቹ ጠባይ መጥፎ ነው:: ወደ ዋሻችን በመጣ ጊዜ 'አሁን ገና አንድ የእውነተኛ አምላክ ተከታይ ጐ ረቤት አገኘን ብለን ነበር::' ከዚያም ጠባያችንን ለማሻሻል ወስነን ነበር:: ግን እኛ ለእርሱና ለባለቤ ልጆቹ አንድ ሁለት ቁም ነገር እናስተምራቸዋለን:: እነርሱ እና የእነርሱ አንድ እውነተኛ አምላክ! ግን እርሱ ስለ ሃይማኖት ከቶ አላነሣም:: ቢናገረን ኖሮ ራሱንና ሴት ልጆቹን እንዲያስተምር በነገርነው ነበር:: አሁን ታዲያ ሎጥና ቤተሰቡ ወደ ሌላ ስፍራ የሄዱ ይመስለኛል:: ወዴት እንደ ሄዱ ማንም



አያውቅም::

«የአብርሃም የሥጋ ዘመድ ነው ይሉታል:: ይህ አብርሃም ልዩ ሰው ነው:: ስለ ሃይማኖት ቢነግረኝ በሰማሁት ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ የሚያስተም ረውን በሕይወቱ ይኖርበታል:: እርሱ በጣም የተከበ ረ ሰው ነው:: እኔ አይቼው አላውቅም፣ ግን የምናገ ረው ሲያወሩ የሰማሁትን ነው::»

«እንዲህ ማለት በእውነት አብርሃም የሄደበትን ስፍራ አታውቅም ማለት ነው?»

«ይኸውልህ፣ አእምሮህን ተጠቀም:: ወደ ተራራ ዎቹ ሄዶ ይሆን? የለም ወደዚያ ከዚያ ሁሉ እንስሳት ጋር አይሄድም:: ለምን የእንስሳቱን ዱካ ተከትለህ ሄደህ ድንኳኖቻቸውን የት እንደ ተከሉ አትፈልግም? በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እኮ ናቸው:: ቀርበህ ማየቱ ብቻ እኮ ይበቃል:: ይልቅስ ባለመሰልቸት ተጓዝ፣ ታገኛቸዋለህ:: ሰዎች እውነተኛውን ነገር ስለማይናገሩ እኛ ሰዎችን አንጠይቅም:: ስለዚህ ራስህ ለፍተህ ማግኘት አለብህ::»

«የእኔ ወዳጆች እንደዚህ አይደሉም፣» አልኩ::

«አንተ ዕድለኛ ነህ፣ እኛ ወዳጆች የሉንም:: እርሱና እኔ ብቻ ነን:: ስለዚህ የምንፈልገውን ምግባችንንም ሆነ ሌላ ነገር የምናገኘው በራሳችን ጥ

ረት ነው።»

በቃ ይኼው ነው!

ግን አብርሃምና ልዕልት ሣራ የት ናቸው? እኔ እነርሱን ፍለጋ የብዙ ኪሎ ሜትር ርቀት መጓዝ አልችልም። ያሉበትን እስከምሰማ ድረስ ወደ ቤቴ ብሄድ ይሻለኛል ብዬ አሰብኩ።

ከዚህ በኋላ ያን ባዶ የሆነ ስፍራ ትቼ ሄድኩ።



እግረ መንገዴን፣ አንድ የተጫነ አህያ እየሳበ የሚሄድ ሰው አገኘሁ። አሁንም ያን አዳህ የሰጠችኝን የወንድ ልብስ መልበሴ ጠቀመኝ። ስለዚህ ዘና ብዬ ይህን እንግዳ የመጀመሪያውን ጥያቄ እንዲህ ብዬ



መጠየቅ ቻልኩ።

«አብርሃምና አብረውት ያሉ ሰዎች ሁሉ ወዴት እንደ ሄዱ ታውቃለህ?»

«የሄደው በቀጥታ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ነው። ልነግርህ የምችለው ይህንኑ ብቻ ነው፣» አለና ሰውዬው፣ «ከጥፋቱ በኋላ ይህ ስፍራ በአመድና በድኝ በሌላም ነገር ስለ ተሞላ፣ ከጥፋቱ በኋላ ስፍራው ለእንስሳቱ አመቺ አልሆነም። እንስሳቱ ቢቆዩ ኖሮ ይታመሙ ነበር። ስለዚህ ያላቸውን ሁሉ ጭነውና ይዘው ወደ ምዕራብ ተጓዙ። እኔ የማውቀው ይህንኑ ብቻ ነው።»

«አሁን የሚኖሩበትን ስፍራ ስም ታውቃለህ?» ብዬ ጠየቅሁት።

«በፍጹም አላውቅም። ግን ቆይ እስቲ። ከአቤ ሜሌክ ጋር አልተግባቡም፣ ሲጨቃጨቁ ነበር ሲሉ ሰምቻለሁ። አቤሜሌክ የጌሬራ ንጉሥ ነው። ይህም የፍልስጥኤም አገር ነው፣ ታውቃለህ? ያለመግባባቱ የተከሰተው በአብርሃም ሚስት በሣራ ምክንያት ነበር። ምንም እንኳን ባይኔ ባላያትም ውብ ሴት ናት ይላሉ። ንጉሥ አቤሜሌክም ሊያገባት ፈልጐ ነበር። ይህንንም ያደረገው ሣራ የአብርሃም እኅት መስላው ነው። ከዚያም ወደ ቤተ መንግሥቱ ወሰዳት።»

«በድጋሚ! ይህ እንደ ሆነ አትንገረኝ፣» አልኩት።

ሰውዬውም እንደ ጉድ አየኝና፣ «እኔም ከዚህ በላይ ደግሜ ልነግርህ አልችልም! ሻሎም! (ሰላም!)» ብሎኝ ወደ አህያው አመራ::

ስለ ልዕልት ሦራና ስለ ትንሹ ልጅዋ ይስሐቅ በጣም አሰብኩ:: ለረጅም ጊዜ ከቆየሁ በኋላ፣ ስለ ወዳጄ ስለ ልዕልት ሦራ እውነተኛውን ዜና ከየት አገኛለሁ? በማለት ተጨነቅሁ:: ይህ ታሪክ እውነት ከሆነ አብርሃም እብድ ይሆናል::

አሁን ዜናውን የነገረኝ ሰው ሽማግሌ ነበር:: ስለዚህ ምናልባት ልዕልት ሦራ በግብፅ ቤተ መንግሥት ተወስዳ እንደ ነበረ ካጫወተችኝ ታሪክ ጋር ያሁኑን ሳያደባልቀው አልቀረም::

ልክ ነው! ሰውዬው ታሪኩን ያምታታ ይመስላል:: ምን ዓይነት የፍልስጥኤም ንጉሥ ነው፣ የዘጠና ዓመት አሮጊት ማግባት የሚፈልግ፣ ደግሞም እርሷ. . . . የደረሰች ናት::

ኋላም ይህ ሁሉ ሰበብ የፖለቲካ መሆኑን አስታወስኩ:: አብርሃም አሁን ሀብታም ሰው ስለሆነ፣ ምናልባት አቤሜሌክ ይህን ጋብቻ እንደ ሰላም ስምምነት ቆጥሮት ይሆናል:: ከዚህም በተጨማሪ፣ ገዢዎች ሚስቶቻቸውን ለማግባት ሲሉ ባሎቻቸውን ይገድላሉ:: ምስኪን ልዕልት ሦራ! ምስኪን አብርሃም!


ለመሆኑ ምን እንደ ደረሰባቸውና የት እንደሚገኙ



የሚነግረኝ አንድ ሰው እንኳ የለም?»

በጭንቀት አሳብ ተውጬ መሬት መሬቱን እያየሁ ስሄድ፣ ሌላ መንገደኛ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ እኔ ሲመጣ አልታየኝም ነበር:: አህያው ከእኔ ጋር ለትንሽ ተጋጭታ ነበር:: ምስኪን እንስሳ፣ ከጌታዋ ጋር ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ተሸክማ ነበር:: ለመከራ የተፈጠረች እንስሳ!

«ኧረ፣ እዛ ጋ! ሰውየው መንገድህን እያየህ ሂድ!» አለኝ::



«እኔም እኔን ነው የሚናገረው ወይስ አህያዋን? አልኩ::

«እኔም ይቅርታ አዝናለሁ» አልኩና፣ «አብርሃምና ልዕልት ሦራ ወዴት እንደ ሄዱ ታውቃለህ?» አልኩት::

«ከዚህ ወዴት እንደ ሄዱ አላውቅም:: ነገር ግን በቤርሳቤህ እንደ ተቀመጡ ወሬ ሰምቻለሁ:: አብርሃም በዚያ ስፍራ ብዙ ዛፎችን ስለ ተከለ እዚያው ሳይቆዩ አይቀሩም:: ብዙ የዝግባ ዛፎችን ተክሏል:: የዝግባ ዛፎችን ይወዳል መሰለኝ:: ኧረ እንዲያውም ለአምላኩ መሠዊያም ሠርቷል:: እነዚህ ሁሉ በዚያ የመቆየታቸው ምልክቶች ናቸው::»

«ባለቤቱ ደህና ነች?» ብዬ ጠየቅሁት::

«አዎ፣ ደህና ናት:: እንዲያውም የሆነውን ሰምተሃል? ባለቤቱ እኮ ልጅ ወለደች!»

«እውነት? ልዕልት ሦራ?»

«አዎ፣ ነገሩ አስገራሚ ከመሆኑ የተነሣ፣ የሰው ሁሉ መነጋገሪያ ሆኗል:: እርሷንም ቢሆን ነገሩ እያሳቃት ነው አሉ:: ልጅዋን ይስሐቅ ብላ ሰይማዋለች፤ ትርጉሙም «የሚያስቅ» ማለት ነው:: በዚያ ሰፈር ሁሉም ሰው ተደንቋል:: እርሷ ዘጠና ዓመት ሲሆናት፣ ባሏ ደግሞ የመቶ ዓመት አዛውንት ነበር:: መቼም የግርምት ማለቂያ የለውም! ሁሉንም ነገር አሁን ሰማሁት:: ቢሆንም፣ በዚህ ዕድሜ ልጅ መውለድ የሚፈልግ ሰው የለም:: እነርሱ ግን



ሕይወታቸውን ሙሉ ልጅ ለመውለድ ሲመኙ ቆይተዋል:: እንደሚባለው የአብርሃም አምላክ በነገሩ አለበት:: ወጣትነታቸውን መልሶ ሰጣቸው:: ሚስቱ ይህን ሁሉ ዘመን ውበትዋ አልረገፈም ነበር ይላሉ::»

ሰውዬው እንደገና መሳቅ ጀመረ:: «እዚያ አገር ታዲያ አንድ ንጉሥ ሊያገባት ፈልጎ ነበር:: በዘጠና ዓመት? ጉድ ነው!» አለ::


«ይህ የምትለው ነገር እኮ ከረጅም ዓመት በፊት፣ ማለቴም ከሃያ ዓመት በፊት፣ በግብፅ አገር የሆነ ነገር ነው::»

«ምንድን ነው የምትለው? ያኔም ሆኖ ነበር እንዴ? በእርግጠኝነት፣ እዚያ በፍልስጥኤም ይህ ሆኖ ነበር:: የተምታታ ነገር አለ:: ንጉሡ አላገባትም:: የአብርሃም ሚስት መሆንዋን ባውቅ ኖሮ እንኳን ሁለቴ አልመለከታትም ነበር ብሏል:: ግን ሁለቱም፣ አብርሃምም ሦራም የአብርሃም እኅት መሆንዋን ነበር የተናገሩት:: ታዲያ እነርሱ እንደዚህ ካሉ፣ ንጉሥ አቤሜሌክ ነገሩን እንዴት ይወቅ? ንጉሡ እኮ ጥፋተኛ አይደለም:: በዚህ ምክንያት ነበር ንጉሡ እንዳይሳሳት እግዚአብሔር በሕልም ታይቶ ያስጠነቀቀው:: እንዲሁም፣ ሦራን ቢነካ እንደሚሞት እግዚአብሔር አስጠንቅቆታል:: ያ አቤሜሌክን

አስደነገጠው::» አለና መንገደኛው ራሱን ነቀነቀ::

ምንም ነገር ለመናገር አፈርኩ::

«ሆኖም፣ ነገሩ ሁሉ በሰላም አለቀ:: አቤሜሌክ ሦራን መልሶ ለአብርሃም ሰጠው:: ይህን ባደረገ ጊዜም መልካም ነገር ነገራቸው:: እንዲህ አለ፡- ያደረጉትን በትክክል ሳይነግሩት በመቅረታቸው መሳሳታቸውን ነገራቸው:: ከዚያም አብርሃምን ስጦታዎችን አስታቀፈው:: ብዙ የበግ መንጋ፣ የቀንድ ከብቶች፣ አገልጋዮች፣ ብዙ ከረጢት ብር ሰጠው:: ይህንንም ያደረገው ሚስቱን ለመውሰድ ስለ ሞከረ የከፈለው ካሣ ነበር:: እንዲያውም ለአብርሃም በአገሩ ውስጥ በመረጠው ስፍራ መኖር እንደሚችል ነገረው:: ንጉሡ ቸር ሰው ነው!»





ራሴን ብነቀንቅም፣ ምን ማለት እንዳለብኝ ግን አላውቅም ነበር::

መንገደኛውም ቀጠለና፣ «የአቤሜሌክ ሚስትና አገልጋዮች ልጆች እንዲወልዱ፣ አብርሃም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ:: ይህም አቤሜሌክ ሦራን በመውሰዱ ምክንያት እግዚአብሔር የሴቶቹን ማኅፀን ዘግቶ ስለ ነበር ነው::»

ይሄ የሦራን ሕፃን አሳሰበኝ:: የነገሩን ርእስ በመለወጥ፣ «እናም ልዕልት ሦራ ልጅ ወለደች!» አልኩ::

«አዎ፣ ውብ የሆነ ትንሽዬ ልጅ ወለደች::»

«እርሷንና ልጇን ለማየት መሄድ አለብኝ፤» አልኩና ወዲያው ጉዞዬን ቀጠልኩ::

ስለ አብርሃም እና ሣራ <u>አብርሃም፣ የእግዚአብሔር ወዳጅ</u> ከተባለው የወይዘሮ ጂ. ቀጣይ መጽሐፍ ውስጥ አንብቡ::

## ታስታውሳላችሁ . . . ?

ምዕራፍ 1:: የአብርሃም ቤተ ሰቦች

1. አብርሃም የሚኖረው የት ነበር?

2. እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ አብርሃም የሚኖረው የት ነበር?

3. የአብርሃምና የአጋር ወንድ ልጅ ስሙ ማን ነበር?

ምዕራፍ 2:: የእስማኤል ታላላቅ ተስፋዎች

1. አጋር የመጣችው ከየት አገር ነበር?

2. እግዚአብሔር እስማኤል ከመወለዱ በፊት ለአጋር ምን ተስፋ ሰጣት?

3. አብርሃም ሎጥን ያዳነው እንዴት ነበር?

4. አብርሃም ለመልከ ጼዴቅ ምን ሰጠው?

ምዕራፍ 3:: አብርሃም፣ የእግዚአብሔር ፈር ቀዳጅ

1. እግዚአብሔር ለአብርሃም በካራን ምን ተስፋ ሰጠው?



2. እግዚአብሔር ለአብርሃም በሴኬም ምን ተስፋ ሰጠው?

3. አብርሃም በሴኬም ምን ሠራ?

ምዕራፍ 4:: የልዕልት ሦራ ስሕተት

1. አብርሃምና ሦራ ወደ ግብፅ ለምን ሄዱ?

2. አብርሃምና ሦራ በግብፅ የዋሹት ውሸት ምን ነበር?

3. ፈርዖን ውሸት እንደ ተነገረው ባወቀ ጊዜ ምን አደ ረገ?

4. አጋር ልጅ እንድትወልድ ሦራ ለምን ፈለገች?

ምዕራፍ 5:: የሎጥ ምርጫ

1. ሎጥ የት ይኖር ነበር?

2. አብርሃምና ሎጥ አብረው መኖር ለምን ተዉ?

3. አብርሃም ሎጥን ምን ምርጫ እንዲያደርግ ፈቀደለት?

## ምዕራፍ 6:: የአብርሃም እንግዶች

1. አብርሃም ለእንግዶቹ ምን አደረገ?

2. እንግዶቹ ለአብርሃምና ለሦራ ምን ተስፋ ሰጡዋቸው?

3. እንግዶቹ በምን ምክንያት ነበር ወደ ሰዶም የሄዱት?

## ምዕራፍ 7:: የሁለቱ ከተሞች አስፈሪ ወግ

1. ሰዶምና ገሞራ እንዴት ወደሙ?

2. ከሰዶም ማን ተረፈ (አመለጠ)?

3. በሎጥ ሚስት ላይ ምን ደረሰባት?

## ምዕራፍ 8:: አብርሃም ሰፈሩን ነቅሎ ተጓዘ

1. ሎጥና ሴት ልጆቹ ወዴት ሊኖሩ ሄዱ?

2. አብርሃምና ሦራ ለንጉሥ አቤሜሌክ የነገሩት ውሸት ምን ነበር?

3. አብርሃምና ሦራ ለልጃቸው ምን የሚባል ስም አወጡለት?

---



# አብርሃም፣ የእግዚአብሔር ወዳጅ

«በተአምር ስለ ወለድነው ሕፃን ምን ታስቢያለሽ? ብሎ ጠየቀ::

«አስደናቂ የሆነ ትንሽዬ ልጅ ነው!» አልኩት።

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ፈጸመለት:: ስለዚህ ሕፃን ይስሐቅም ተወለደ:: በቅርብ ግን አንድ ኃይለኛ ውሳኔ መወሰን ይኖርበታል:: ይህ ውሳኔ ደግሞ ለሕይወቱ አደገኛ ነበር! ይህን ወይዘሮ ጂ. ስለ አብርሃም በጻፉት ሁለተኛው መጽሐፋቸው ውስጥ ቀጥላችሁ አንብቡ::

ከዚህ ቀደም በጸሐፊዋ የተዘጋጁ መጻሕፍት:-

1. አዳምና ሔዋን

2. ኖኅ